
# ምእራፍ ስድስት

## ክርስቲያናዊው ዘመን አቆጣጠርና
## መንደርሪያው የሥነ - መለኮት ትምህርት

ክርስቲያናዊው ዘመን እንዲሁም አቆጣጠር (Chrishan era and calendar) መንደርደሪያውና መሠረቱ ጅማሬውና ትምህርቱ ሁሉ የሚነሳው ከአምላካችን ከጌታችን ከመድሐኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ነው:: ይህንን አስመልክቶ ክርስትና አለምን የማሸነፍዋ ነገር ተደምሮበት በምእራቡ አለም በቅዱስ ቆስጠንጢኖስ አዋጅ (Edict of Millan) ክርስትና እውቅና ስታገኝ ብቻ ተቀባይነት ያገኘ ሲሆን ወደ ክርስቲያናዊው ዘመን መቁጠሪያ ምዕራባውያኑ መምጣት እንዳለባቸውም የጭላንጭል ያህል በአምሮአቸው ተስምቷቸው ነበር:: የግብፅ፣ የኢትዮጵያ፣ የህንድ እና የሶሪያ ክርስቲያኖች ደግሞ ከሐዋሪያቱ ስብከት ጀምሮ የዘመናት መከፈያ በሆነው በጌታችን፣ በአምላካችን፣ በመድሐኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ልደት እንዲቆጥሩ በክርስቲያን መንጋ ላይ የተሸሙት ሐዋሪያት አበው እንዲሁም ጳጳሳት በሙሉ የአዲስ ዘመን መጀመሪያና የአሮጌው እና የጥላው ዘመን ማሳለፊያ አድርገው የዘመን ሥርአትን ስርተዋል::



በዚህም የተነሳ በአለም ላይ ያሉት ሊቃውንት ሁሉ ይህንን የጌታን ልደት የክርስቲያን ዘመን መጀመሪያ /beginnings of Christian era/ በማለት ጠርተውታል የጌታችን መወለድ በክርስትና ትምህርት ውስጥ ሁለት ዘመኖችን የከፈለ አሮጌውን በአዲስ የተካ አለም አቀፋዊ ለውጥ ነው:: በዚህ በክርስቲያናዊው እምነት የዘመን አቆጣጠር ፅንስ ሃሳብ ላይ የተመሰረቱ የአለም ዘመን መቁጠሪያዎች ሁሉ ይህንኑ የሚያመላክቱና የሚገልፁ ቋንቋና ቃላት /terms/ ያሏቸው ናቸው:: እንደ ምእራብያውያን ልማድ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ እንዲሁም ዘመነ እግዚእ /Before Christ and anno domini which means in the year of our lord/ በመባል ይህ የዘመናት እኩል ክፍያ ሲታወቅ እንደ ኦርቶዶክሳወያኑ ሐዋርያዊ ትምህርት ግን ዘመነ ኩነኔ /ፍዳ/፣ ብሉይ ኪዳን የሚባለውና ሰፊ ሽፋን ያለው ክፍያ ጋራ ዘመነ ሐዲስ ወይም ምህረት በመባል የሚታወቀውን የያዘ እንደሆነ ይታወቃል::




ማመልከቻ 1. በዘመን መስመር (time line) ላይ የተመሰረተ የምዕራቡ አለምና የኦርቶዶክሳዊያኑ ዘመን አቆጣጠር መደርደሪያ ስነ መለኮታዊ ትምህርት ልዩነት የሚያሳይ


በማመልካቻው ላይ ያለው የዘመን መሥመር (time line) ከፍጥረተ አለም የሚነሳ እንደሆነ እና በህልፈተ አለም የሚገደብ ተደርጐ ውሱን መሥመር ሊሆን ያስችለዋል:: ምእራብያኑ በሚያመልኩት ደረጃ ሳይንሳዊውና ክርስቲያናዊው የተቀላቀለባቸው ማህበረሰብ ስለሆኑ ለፍጥረተ አለም መጀመሪያ የለውም የሚለውን ሀሳባቸውን ቀጣዩ ጨረር ያመለክታል:: ይህ አመለከከት ቁስ አካላዊ /materialists/ እንደሁም ዘገምተኛ ለውጣዊ /evolutionist/ ሲሆን ክርስቲያናዊ የሥነ መለኮት ትምህርትን የማይወክል እንደሚያደርገው ግልጽ ነው:: ለማንኛውም የክርስቲያናዊው ዘመን መቁጠሪያ ሊይዛቸው የግድ የሚገቡ የሚባሉትን መረጃዎችና አመቶች እንዲሁም ታሪኮች ከመጽሀፍ ቅዱስ መነሻነት እንዳስሰዋለን::

ይህንን ከማድረግ በፊት ግን ይህ የኦርቶዶክሶች ባህልና ባሕረ ሐሳብ ልማድ የሚያዘው ትምህርትና መንደርደሪያ እንጂ ምዕራባውያኑ ካቶሊካውያኑ ቢሉ ፕሮቴስታንታውያኑ የማይቀበሉት አካሄድ ነው እንደ ምዕራባውያኑ ከካቶሊካውያኑ ቢሉ ፕሮቴስታንታውያኑ ሌሎቹም ክፍሎች አስተያየት መጽሀፍ ቅዱስ ማስረጃነቱ ጊዜያዊ፣ ህፀፃዊና፣ መረጃ አልባ ሲሆን እንደኛ ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ ገላጭነት በእግዚአብሔር ፍቃድ ያለ ስህተት ያለ እንከን በፍፁም እውነትነቱ እና



በመጨረሻ ወሳኝ ማስረጃነቱን ይዘን ለማናቸውም ጥያቄና ምላሽ ማመሳከሪያም አድርገን እንታመንበታለን::

በዘመን አቆጣጠር ላይ ያለው የምእራብያኑና የኦርየንታል ኦርቶዶክሶች አለመግባባት የሚመነጨው ከዚሁ ዋና አንኳር ሃሳብ እንጂ ከሌላ አይደለም:: «መፀሀፍ ቅዱስ ይወስን» ብለን ለምንጠይቃቸው እንዲሁም መረጃ አድርገን ለምናቀርባቸው ክርክሮች/Arguments/ መልሶቻቸው ሁል ጊዜ «መፀሀፍ ቅዱስ ስህተት አለው» በሚል የክህደትና የምፍቅና መልስ ስለሚቋጩት ነው:: ይህ እንዳለ ሆኖ የኦርቶዶክሶቹ የክርስቲያን የዘመን መሥመር ከመፀሀፍ ቅዱስ ማስረጃነት አንፃር ምን እንዳሆነ እንመልከት::




ማመልከቻ 2:- የኦርቶዶክሱ የመጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃና የዘመን መቁጠሪያ መንደርደሪያ ድንበር የሚያሳይ የዘመን መስመር

ክርስቲያነዊው የዘመን አቆጣጠር በዋነኛነት ከላይ የተዘረዘሩትን ሁሉ የሥነ - መለኮት ትምህርታዊና መፀሀፍ ቅዱሳዊ መረጃዎች ያሞላ መሆን ይገባዋል:: እነዚህን

አመቶችን እና መረጃዎችን ከግልጽ ገለፃ ጋር ያልያዘ ዘመን አቆጣጠር ሙሉ በሙሉ ኢ-ክርስቲያናዊ ስለሆነ ወይም ክርስቲያናዊ ስላይደለ እንደ ማናቸውም በአለም ላይ ያለ እራሱን የቻለ ዘመን መቁጠሪያ ሊያዝ ይገባዋል:: ስለሆነም በአሁኑ ሰዓት ቻይና፣ ጃፓን፣ ህንድ እና እስላማዊ ሀገሮች እንዲሁም ጥንታዊ ሥልጣኔዎችና አይሁድ የራሳቸውን ዘመን መቁጠሪያ ይዘው ሲጓዙ ይታያል:: ወደ ቀደመው ነገር ስንመለስ ከላይ በተዘረዘረው ሁናቴ መጽሀፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎችን ብሎም ድንበሮችን ያካተተ ማንኛቸውም ዘመን አቆጣጠር ክርስቲያናዊ ለመባል በሚከተለው ሁኔታ መረጃዎቹን መተንተን ይገባዋል:: በመጀመሪያ ደረጃ ዘመን መቁጠሪያ ሁሉ ከጌታችን ከክርስቶስ ልደት በመነሳት የአለምን ዘመን ለሁለት መክፈል ይገባዋል በሚል መደርደሪያ ይነሳል በማስቀጠልም፣

ሀ. ስለ ጌታችን ልደት የሚያወሳው መረጃ ካለ በመጽሀፍ ቅዱስ የተጠቀሰውን የጌታችን በቤተልሔም በከብቶች በረት የመወለዱን ታሪክ የያዘ መሆን አለበት:: ወራቱም በራድ ከመሆኑ አልፎ አምላክ ከናዝሬት ወደ ቤተልሔም ድረስ እመቤታችን ተጉዛ እንደወለደችው መፀሀፍ ቅዱስ እስከ ምክንያቱ በዝርዝር ይገልፃል:: ይኸውም አስቀድሞ ያናገረው የትንቢት ቃል ይፈፀም ዘንድ «ቤተልሔም ከይሁዳ ከነገስታት



ሀገር ከቶ አታንሺም ልዑል ካንቺ ይወለዳልና» የሚለው ይፈፀም ዘንድ በቤተልሔም ተወልዶአል:: (ትንቢ. ሚኪ. 5:2) አለማዊው ሂደት ደግሞ በዘመኑ ቄሳር ከነበረው ከአውጉስጦስ (አክቴቪያን) ዘንድ ሰው ሁሉ ይፃፍ (ይቆጠር) ዘንድ ትእዛዝ (አዋጅ) ስላወጣ ቄሬኔዎስ ደጀዝማች በነበረበት ወቅት የእስራኤል ሰው ወደየ ወገኑ ከተማ (የይሁዳ ወደ ዳዊት ከተማ ቤተልሔም) የሌሎቹም ወደየ ወገኖቻቸው (አበው እስራኤል) በመሰረቱት ከተሞች ዘንድ እየሔዱ እንዲቆጠሩ በማስገደዱ ከይሁዳ ወገን የነበሩት ዮሴፍ አረጋዊ እና እመቤታችን ወደ ቤተልሔም ሊቆጠሩ መጡ በዚያም ዘመን እመቤታችን የመውለጃዋ ወራት ገብቶ ነበርና ጌታን በቤተልሔም የከብቶች በረት በነበረችው ዋሻ ወለደችው የሚለውን ታሪክ እናነባለን (ሉቃስ 2:1)

ሌላው ማስረጃ ደግሞ በቤተልሔም ከምሥራቅ የመጡ ነገስታት ከ300 ጭፍሮቻቸው ጋር ወደ ጌታ ዘንድ እንደቀረቡ በጥበብም መንፈሳዊ የተቃኙ በመሆናቸው ስብአ ሰገል ሲል መጽሀፍ ቅዱስ እንደሰየማቸው እነርሱም ጌታ አርባ ቀን ሞልቶት የእርግብ ጫጩቶችን እንደ ኦሪቱ ሥርዓት ሊሰዋ በእመቤታችን እቅፍ ከመሄዱ በፊት መሆኑን እንረዳለን ሰብዓ ሰገል በቤተልሔም አግኝተውታልና ወደ ኢየሩሳሌም ሳይወርድ ገና ከአርባ ቀን በፊት ደርሰዋል:: (ማቴ 2:8-12) (አንድምታ ወንጌል ዘማቴዎስ)

ለ. ሁለተኛው መረጃ ከጌታ ልደት በኋላ የሄሮድስ ሰይጣናዊ ቁጣ እንደተቀጣጠለ ይኸውም የአይሁድ ንጉስ ወዴት ተወልዷል እያሉ ከምርጥ ጀግኖች ጋር የመጡትን ሰብአ ሰገል ነገስታተ ፋርስን በድንጋጤ ያየው ሄሮድስ ከእነርሱ በተንኮልና በሚያባብል ቃል ስለ ተወለደው ንጉስ እየመረመረ ኮከቡ የታየበትን ዘመን በጥንቃቄ ከተረዳ በኋላ ሁለት አመት እንዳሆነ አወቀ:: ሰብአ ሰገልም በሁለት አመት ጊዜ ከሀገራቸው ተነስተው በኮከቡ እየተመሩ ብዙ እርቀትን ብዙ ጋሬጣን አልፈው ከምርጥ ጀግኖቻቸው እና ጨዋዎች ጋር እየተመሙ መድረሳቸውን ተረዳ::

በዘመኑም ሄሮድስ ስልጣኑን ለማደላደል ሲል ከሮሜ መንግስት ጋር ሆኖ የአይሁድ ስልጣን ተጋሪዎቹን ሲዋጋ ሰንብቶ ኖሮ የእርሱም ተከታዮች ተራውም ህዝብ ጦርነት ሰልችቷቸውና ጠንክሮባቸው ነበርና «ከአለም ዳርቻ እኚህን ሃይለኞች የጠራ እኔን መች ያስነብተኛል» ብሎ ተጨነቀ:: አሁን ብቃወመው እነዚህ ያጠፉናል ይገድሉናል ሲል ሲፈራ ሲተባ ቆይቶ እኔም እንድሰግድለት ካያችሁት በኋላ ንገሩኝ በማለት ዘይዶ ሊያስወግደው አቅዶ ነበር:: ነገር ግን ሳይመጡ በቀሩበት ጊዜ እንደተሳለቁበት ተረድቶ ሰይጣናዊው ቁጣው ተቀጣጠለ::

በዚህም የጌታችን ስደት መጀመሩን በስደቱም ለ3 አመት ከ6 ወር በግብጽና በኢትዮጵያ መዘዋወሩን በዮሐ.እራይ



12:13 -16 ላይ ተፅፎ እንረዳለን:: በዚህ የመፀሀፍ ቅዱስ ገፅ ንባብ ሚስጥሩ ሲፈታ ወንድ ልጅ የወለደችውንም ዘንዶው ተቆጥቶ ሊያጠፉ አሳደዳት (ለጊዜው ሄሮድስ በቁሙ ግን ዲያቢሎስ):- የታላቁ የንስር ክንፍ ተሰጣት እያለ ሲዘረዝር የሄሮድስ ወታደሮች ጌታን ለመግደል የቤተልሔምን አውራጃ እንደበረበሩ ወደ ግብፅም መሔዱን ሰምተው እንደ ተከታተሉት የጌታ መላእክም በለሊት በህልሙ ለዮሴፍ እንደተገለፀ ከፊት እየመራ ከኋላ እየጋረደ እንደተሰደዱ ሲገልጽ ዘንዶውም በኋላዋ ታላቅ ጐርፍን አጐረፈ ሲል በቤተልሔም የፈሰሰውን 144 ሺህ ህፃናት ደም ይገልፃል:: ከእባቡም ፊት ርቃ አንድ ዘመን፣ ዘመናትም፣ የዘመን እኩሌታ ወደ ምትመገብበት ወደ ስፍራዋ ወደ በረሃ እንድትበር የታላቁ ንሥር ክንፍ ተስጣት በዚያም ቆየችም ይለናል::

ሐ. ጌታችን የስደቱ ዘመን አልቆ ወደ ምድረ እስራኤል በመጣ ጊዜ በ12 አመቱ ወደ ቤተመቅደስ ገብቶ ከእናቱ ተለይቶ ለአራት ቀን የኦሪትን ሊቃውንት እና ሊቀ ካህናት ሲጠይቅና ሲያስረዳቸው ሚስጢር ሲገልጥላቸውና ማንነቱን ይረዱ ዘንድ ሲያመለክታቸው ያለውን ታሪክ እናነባለን:: (ሉቃ 2:42)

መ. ጌታችን ጊዜው ደርሶ ወደ አለም የመጣበትና የድህነት ሥራ በእጆቹ ታምራት እያፀና በአፉ ትምህርት እያቀና የሚሰብክበት በግልጽ ለህዝብ የሚታይበት ስአት

በደረሰች ጊዜ በይሁዳ ምድር ወደ ነበረው ወደ ዮርዳኖስ ባህር መጣ በዚያም የጌታን መንገድ እየጠረገ ህዝቡ ሁሉ ለወንጌል ትምህርት ልባናውን ያቀና ዘንድ የታዘዘው ንፁሁ ዮሐንስ መጥምቀ መለኮት ነበር:: ጌታም ወደ ዮርዳኖስ ባህር በመጣ ጊዜ እድሜው 30 አመት ሆኖ ነበር:: ወንጌል ይህንን ሲያስረዳ «ኢየሱስም ሊያስተምር ሲጀምር እድሜው ሠላሳ አመት ሆኖ ነበር »ይላል (ሉቃስ 3:23)

ሠ. ጌታችን መጽሐኒታችን መላዋን እሥራኤልን ለ3 አመት ከ3 ወር ከሀገር ሀገር እየተዘዋወረ ያስተማረበት የድህነትና የምህረቱን ነገር ሊፈጽምልን ጊዜው ሲደርስ አዳም ሊቀጣ በሚገባው ቅጣት ካሳ እራሱን ስጥቶ በሞቱ ከሲኦል ውስጥ እና ከአጋንንት እግር በታች ተጠቅጥቀን እንኖር የነበርነውን የሰውን ልጆች በታላቅ ሃይል መንግስቱን የምንወርስበትን ከመከራ እና ከፍዳ (ከሲኦል) ነፃ የወጣንበትን ትንሳኤውን ሰጠን:: ይህም በመፅሀፍ ቅዱስ ተመዝገቦአል:: ይህንን ዘመን በዋና ማስረጃነቱ በመያዝ ተያያዥ ታሪኮችን ደግሞ በማመሳከር በጌታችን ዘመን ከተነሱ የታሪክ ፀሀፊዎች ሥራ ጋር በማያያዝ ስለ ክርስቲያናዊው የዘመን አቆጣጠር ከብዙ በከፊልና በዝርዝር መናገር ያስችላል::

መፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተመዝግቦ ለታሪክ ማነፃፀሪያ ከሆኑት አበይት ምልክታዎች መካከል ጥቂቱን ስንመለከት ወሳኝ የሆኑ ድንበሮችን በዘመን መስመር ላይ በማስቀመጥ



የምንዘግበው ስለ ዘመን አቆጣጠር ከኢ-ክርስቲያናዊው የአለም ታሪክ ሂደት ጋር በተለየ መልኩ ስላለው ሁኔታ በይበልጥ እንድንገነዘብበት ነው:: ለምሳሌም ያህል የሚከተሉት ታሪካዊ ክንውኖች ስለ ክርስቲያናዊው ዘመን መቁጠሪያ ታሪካዊ ማመሳከሪያ በመሆን ፍንጭ ይሰጣሉ::

ሀ. የጌታችን የስደት መልስ «ከሞተ ሄሮድስ» ጋር መያያዙ በሚገባ ተዘግቧል:: በወንጌል ማቴ2:19 እንደተፃፈው ሄሮድስም ከሞተ በኋላ እነሆ የጌታ መልአክ በግብፅ ለዮሴፍ በሕልም ታይቶ «የሕፃኑ ነፍስ የፈለጉት ሞተዋልና ተነሣ ሕፃኑን እናቱንም ይዘህ ወደ እስራኤል አገር ሂድ አለው» ይላል:: ይህም ሄሮድስ ልክ ሲሞት ጌታችን ከግብፅና ከኢትዮጵያ ስደት የመመለሱን ጉዞ ጅማሬ እንረዳለን::

ለ. በተያያዥ ከሄሮድስ ሞት በኋላ ልጁ አርኬላዎስ በመንገሱ «የክፉ ልጅ ክፉ» እንዲል እንድምታው በይሁዳ ይቀመጥ ዘንድ አልወደደም ወደ ናዝሬትም ሄዶ ተቀመጠ:: ሲል (ማቴ 1:22-23) ታሪካዊውን ሂደት ይገልፃል ከሄሮድስ ሞት በኋላ በልጁ አርኬላዎስ አገዛዝ ወይንም ንግሥና ጌታ ከስደት መመለሱን በቀጥታም ናዝሬት መግባቱን እንረዳለን

ሐ. በቤተክርስቲያናችን ታላቅ ሚስጥር ጓዳነት ብቻ የተጻፈ በዓለም የተቃጠሉ እና የተበረበሩ እንዲሁም የተመዘበሩ የሃዋርያት መፃህፍት ሲጠፉ በእኛ የዳኑት ጌታ ናዝሬት ሲገባ ወይም የእድሜው ነገር ከልደቱ ጀምሮ እስከ እርገቱ የሚናገረው ላይ ስንት እድሜ እንደለው የሂደቱንና የታሪኩን ይዘት ሳይዘባርቅ በትክክል ያስቀምጠዋል:: (ተአምር ኢየሱስን ተመልከት)

ተአምረ ኢየሱስ ጌታ ናዝሬት ሲገባ 5 ዓመቱ ነበር ይለዋል (ምዕራፍ 8 ተመልከት) ጌታችን ወደ ግብጽ ሲሰደድ የስድስት ወር ጊዜ በመውሰድ (ይህም ከቤተልሄም እንደ አንድምታው ሳይውል ሳያድር ተሰዶ ግብጽ ሲገባ የሆነውን ሲያመላክት) ከግብጽ ደግሞ እስከ ናዝሬት መንገድ ይርቃልና በይሁዳ ሳይቀመጥ አርኬላዎስ መንገሱን ሰምቶ ይሄዳልና ለስደት ሲነሳ ሁለት ዓመት ቢሆነው ግብጽ ሲወርድ ሁለት አመት ከስድስት ወር ላይ 3 ዓመት ከ6 ወር ሲደመር 6 አመት ሆኖት ናዝሬት ሲገባ ከ6 ዓመት በላይ በደረሰ ነበር:: ስለዚህ ግብጽ ሲደርስ የስድስት ወር ህፃን ነበር የሚለውን ማስተዋል ያስፈልጋል::

ሰልስቱ ሀዲሳት ትርጓሜ እራዕይ ዮሐንስ ገፅ 424 ላይ ግብፅ እመቤታችን ስትሄድ 6 ወር ስትመለስም 6 ወር ወድሶባታል ይላል::



መ. የጌታችን የልደቱ ዘመን በአውጉስጦስ ፣ስቅላቱ ደግሞ በጢባርዮስ ቄሳር ዘመን ስለመሆኑ በግልፅ በወንጌል ተዘግቦአል:: ይህም ማለት በተሳሳተው ግሪጎሪያውያኑ ወይም ዩልዮናዊው ዘመን መቁጠሪያ አውጉስጦስ 27 ቅ.ል.ክ (ሉቃስ:2:2) ጢባርዬስ ደግሞ 14 ዓመተ እግዚእ (ሉቃ3:1) ዘመን ላይ መኖራቸውን ዘግበዋል:: ይህንንም እንዲህ ሲል ይገልፀዋል በዚያም ወራት አለም ሁሉ እንዲፃፍ ከአውግስጦስ ቄሣር ትእዛዝ ወጣች ቄሬኔዎስ በሶርያ አገረ ገዥ በነበረ ጊዜ ይህ የመጀመሪያ ፅሕፈት ሆነ «ጢባርዮስም በነገሠ በአሥራ አምስተኛይቱ ዓመት የእግዚአብሔር ቃል ወደ ዘካርያስ ልጅ ወደ ዮሐንስ መጣ»

ሠ. ጌታችን የተወለደበት ጊዜ በአውጉስጦስ ሰው ሁሉ የሚቆጠርበት (ለግብር የሚፃፍበት) አዋጅ የወጣበት መሆኑ ሌላ ታሪካዊ ሂደት ነው::

ረ. ከጌታችን ልደት በፊት በሮሜ ቅኝ የነበሩት አይሁድ ነፃነትን በመፈለግ በመጀመሪያ በቴዎዳስ በመመራት አመፅ ማስነሳታቸውን ሰዎችም በተፃፉበት ዘመን ወይም በተቆጠሩበት ይህም በጌታ ልደት አመት የገሊላው ይሁዳ ደግሞ ሌላ አመጽ ማስነሣቱ በግልጽ ተዘግቧል:: ይህም ሌላው የታሪክ ምልክታ ሆኖ እናገኛዋለን:: (ሐዋ ሥራ 5:37)

እነዚህን የአለማዊ ታሪክ ፀሀፊዎች የዘገቡትን ጊዜዎች ወይም ዘመኖች አለበለዚያ አመቶችን በማጥናት እና በማገናዘብ ከመፀሀፍ ቅዱስ የጌታችን ዘመን ጋር በማመሳከር ወደ ክርስቲያናዊው ዘመን መቁጠሪያ ላይ መድረስ ይቻላል:: በሚቀጥለው ክፍልም ይህንኑ በመፈፀም የክርስቲያናዊው ዘመን አቆጣጠር እና የዘመን መስመር (time line) ምን እንደሆነ እንረዳበታለን::



## ምእራፍ ሰባት
## የምእራባውያን ዘመን አቆጣጠር አጭር ታሪካዊ አመጣጥ

በአለም ላይ አሉ ከተባሉት ከቀደምት ዘመን መቁጠሪያዎች መካከል ግብፅ፣ ሜሶጳጣሚያ፣ ቻይና፣ ህንድ፣ ጃፓን እና የደቡብ እንዲሁም መካከለኛው አሜሪካ ስልጣኔዎች ተጠቃሽ ናቸው:: ከዚህ ጋር ሊደመር በማይችል መልኩ በጦር ሙያና አደረጃጀት ብቻ እየገነነ የሜዲትራኒያንን አለም ለማስገበር የቻለው የሮሜ ሥልጣኔ ግን ዘመን መቁጠሪያው ከባእድ አምልኮ እና ከወቅት መፈራረቅ ጋር የተያያዘ እጅግ ያልበሰለ ነበር::

በምእራቡ አለም እንኳን ጥንት ዛሬ ድረስ የስልጣኔ መስረታቸው አድርገው በመውሰድ የግሪክ /ፀርእ/ እና የሮሜ ሥልጣኔ ላይ ሲመዓደቁ መስማት በጣም የተለመደ ነው:: ይህ ደግም የዘመን አቆጣጠር ሥርዓታቸውንም ጥንትነት ስንመረምር ከዚያው ተወራሽና ተመሳሳይ ከሆነ ጣኦት አምልኮ የፈለቀ በተረታዊ ትረካዎች የአየር ፀባይና የወቅት መፈራረቅ የሚገልፁበት ክፍል ያለው መሆኑን እንረዳለን:: ለምሳሌ ያህል «የአፖሎ ልጅ በፀሀይ ሰረገላ ላይ ወጥቶ ፈረሶቹን መያዝ ስላልቻለ ዝቅ ብለው በጋለቡበት በረዶው ቀልጦ ደረቅ በረሃ በመሆኑ በድንጋጤ ወደ ላይ በጣም ከፍ ቢያደርጋቸው ወደ

ላይ በመንገዳቸው በሰሜኑ የአለም ክፍል በረዶ የተሸፈነ ሆነ»
እያሉ የማያስተምሩት የጣኦት አምልኮ ሀይማኖት ነበራቸው::

የሮሜ ዘመን መቁጠሪያ ከግሪክ ስልጣኔ የተወረሰ ቢሆንም ቅሉ እንደ ዩልዮሳዊው ዘመን መቁጠሪያ እና አቆጣጠር ከ753 ቅድመ ልደት ክርስቶስ ጀምሮ ያለውን የሮሜ ከተማ ግንባታን እንደ ዘመን መቁጠሪያው መጀመሪያ /Beginning point of a calendar/ መጠቀም የጀመሩ ሲሆን ለብዙ ዘመናት ይህንኑ የዘመን መቁጠሪያ ይዘው ቆይተዋል:: ይህ የሮሜ ዘመን መቁጠሪያ በጨረቃ ኡደት ላይ የተመሰረተና በአስር ወር በኋላም በ12 ወር የተከፋፈለ ነበር:: ይህን በተለያየ ወርና አምልኮ ጋር የተያያዘ ዘመን መቁጠሪያ አስመልክቶ በጥንት ጊዜ ከመካለኛው ምስራቅ ሮማውያኑ የወረሱትም ሊሆን እንደሚችል አንዳንድ ፍንጮች ይጠቁማሉ::

ለምሳሌም ያህል በሮማውያን ስለ ከዋክብት ቆጠራ አስተማሪዎቹ ከቻላይዲያ (Chaldea) የመጡ በመሆናቸው ካላዲያንስ ወይም ቻላዲያንስ በመባል ይጠሩ እንደነበር እነርሱም ስለ ወቅቶች፣ ስለ ከዋክብት አቀማመጥ፣ ያስተምሯቸው እንደነበረ የተዘገበ ነው:: ኋላ ቀሩ የሮማውያን ጥንታዊ ዘመን አቆጣጠር ሌላው የሚታወቀው የመጀሪያው ወር የአመት መባቻው ክረምት ላይ መዋሉ ነው:: ይህ ወር ጃንዋሪ የሚለው አመጣጡ ሮማውያን በብርድ ወራት ከበር



ደጅ የሚኖር መንፈስ አለ ብለው ከማመናቸው የተነሳ ጃነስ (Janus or Sprit of the Door way) በማለት ከሰየሙት ሀረግ የተገኘ ነው:: ይህ ሥረ መሰረቱ በጣኦት አምልኮ ላይ የተንጠላጠለ ተረትና የወቅት ቀመር ዛሬ ድረስ ዘልቆ እንደሚገኝ ማስተዋል ይቻላል:: [1] በአብዛኛው የአለም ክፍል አዲስ አመት ተብሎ የሚታወቀው የፀደይ ወራት እንጂ ክረምት መግቢያ አይደለም:: ይህም በህንድ፣ ቻይና፣ በኢትዮጵያ፣ በእስራኤል እና በግብፅ ተጠቃሽ ነው::

ይህንን የዘመን መቁጠሪያ ይዘው የዘለቁ ሮሜዎቹ በጁሊየስ ቄሳር አማካኝነት ዩልዮሳዊ ዘመን አቆጣጠርን በግብፃዊው ሊቅ በሶሴጅነስ (sosigenes) አማካኝነት የተሰራላቸው በመሆኑ ወደ ተለያየ የአለም ክፍል ይህንኑ የዘመን መቁጠሪያ በቅኝ ሲገዟቸው በነበሩ ህዝቦች ላይ ጭነውታል:: በመሆኑም ለ400 አመታት በባርነት ይገዟቸው የነበሩት እንግሊዛውያን የሮማውያኑን የዘመን መቁጠሪያ እንዳለ ቢወርሱም የጥንት የባዕድና የጣዖት አምልኮ ኋላቀር ዘመን አቆጣጠራቸውን አሾልከው ያገቡበት በመሆኑ ዛሬ ላይ ቆመን ስንመረምር በተጨባጭ ማስረጃ እናረጋግጣለን::

ለምሳሌ ያህል የእንግሊዝ አንግሎሳክስን ጉሳዎች ጠረኛ አማልክቶች ነበሩዋቸው በእነዚህም የያንዳንዷን ቀን ለእነርሱ ግብር የሰጡ በመሆኑ ቀኖቹ ሁሉ በስማቸው ተሰይሞአል:: ለምሳሌ (Mon-day) ሰኞ በጨረቃ (moon- day) ቀን

አስመልክቶ ለጨረቃ ጣኦት የተሰጠ ነበር (Tu's day) ማክሰኞ Tu'S ለሚባል ጣኦት (Weden's-day) እሮቡ woden ለተሳኘ የጦር ጣአት (Thur's –day) ደግሞ ሀሙስ ሆኖ Thor ለሚባል ጠኦት የተለየ ሲሆን Friea's-day በመባል የሚታወቀው አርብ ለዚሁ በተለየ ቀን መስዋት የሚሰውላት የሴት አማልክት መክበሪያ ሲሉ የለዩት በመሆን አገልግሏል:: ለኮከቡ (አለመ ሰማይ) ወይም(planet) saturn ቅዳሜ ሲሰየም የፀሀይ አምልኮን ደግሞ ለማመልከት (Suns-day or Sunday) የሚለውን የSunday መግለጫ ትርጉም ያለው ሆኖ የባዕድ አምልኮ የእምነት ታሪክ እንዳላቸው ፍንጭ ይሰጣል:: ይህንን ሁሉ ሳስተዋለው የዛሬው ምዕራባዊ ዘመን አቆጣጠር ምን ያህል በስልጣኔ ያልበሰለ ማህበረሰብ የፈለቀና የተሰራ እንዲሁም ኢ-ክርስቲያናዊ መሆኑን ማረጋገጥ አያዳግትም::

---

1. See Sergew, p. 200; ________. World history, vol. I USA Armed forces institute (Wisconsin, 1970) p. 124; ምንም እንኳን ይህ የተረጋገጠ ቢሆንም አንደንድ ፀሀፊዎች አውሮፓውያኑ ታህሳስ 28 ተከትለው ጌታ ከተወለደበት አመት ጀምሮ አዲስ አመት መሆን አለበት ብለው ጥርን አዲስ አመት አደረጉት የሚሉት ሀሳብ አለ:: ነገሩ ግን እስከ 1600 አ.እ.ድረስ በእስኮትለንድ እንዱሁም በእንግሊዝ እስከ 1751 አ.እ ድረስ አዲስ ዘመን በመጋቢት March 25 ላይ



ይውል ነበር:: ከላይ ከተጠቀሱት ጊዜዎች ጀምሮ ወደ ጥር (January) ተዘዋውሯል::

ይህ ሁናቴ ቀጥሎ በመጓዝ የጌታችን ልደትን ሁሉ አልፎ የዘለቀው የዩልዮስ ዘመን መቁጠሪያና የሮሜ ቄሳሮች ጣኦት አምልኮና የባእድ አምልኮ ባህል በክርስትና ድል መንሳት አዲስ ምእራፍ ተለውጦ እንዲተካ አስገዳጅ ሁናቴ ተፈጠረ:: ነገሩ የሚጀምረው በቆስጠንጢኖስ የክርስትና ሐይማኖትን ህጋዊነት በሚላኑ አዋጅ በእ.ኤ.አ 313 ላይ የማወጅ ሥራ ነው:: ቆስጠንጢኖስ ይህን መሰል ውሳኔ ሊያሳልፍ የቻለው በ311 ዓ.ም ላይ ለስልጣን ተቀናቃኙ የነበረውን መምልኬ ጣኦት ማክሲመስ እንደ አሸዋ የበዛ ሰራዊት ይዞ ለጦርነት ሊገጥመው በቀረበ ጊዜ በተደረገለት ተአምር የተነሳ ወደ ክርስትና ሃይማኖት የመግባቱን ብፀአት ተከትሎ ነው::

ስለዚሁ ጉዳይ ታሪኩ ሲተረክ ይህን ይመስላል:: ቆስጠንጢኖስ የከበበውን አደጋ ከተረዳ በኋላ ጭንቀትና ውጥረት ናላውን አዙረውት መድረሻ ያጣ ሲመስለው ወደ እናቱ እሌኒ ሀይማኖት አስተውሎ መፀለይ ጀመረ:: ለሊቱንም ታላቅ እራዕይ /ህልም/ ተገለፀለት በሰማይ ላይ ብሩህ የብርሃን መስቀል በጦር ስራዊቱ ላይ እያበራ የእርሱም ጦር ፈረሰኞች እየፋነኑ ሲተሙ ጭንቀትና ፋርሃት ከእርሱ ሲርቅ ተሰማው ታየውም ከመሰቀሉም ውስጥ ታላቅ ድምጽ ወጥቶ ይህንን

ቃል ተናገረው በዚህ መስቀል ምልክትነት አንተ ታሸንፋለህ /In hoc signo vinces/ በጠዋቱም ጦር ሰራዊቱን አስልፎ ሁሉንም በቀይ ቀለም መስቀልን ምልክት በመሳ አካላቸው እንዲያደርጉ አዘዘ በጦርነቱም ጠላቱ ሸሽቶ ሲጋልብ ከታይበር ወንዝ ገብቶ ሰጥሞ ሞተ፡፡ የዚህ ታሪክ መጨረሻው የአፄ ካሌብና እና የፊንሀስ ጦርነት ጋር በመመሳሰል የሚያስደንቅ ነው፡፡



ሥዕል 5፡ ቅዱስ ቆስጠንንጢኖስ ወልደ እሌኒ የተመለከተው እራዕይ የሚያሳይ



የሆነ ሆኖ ከዚህ በኋላ ክርስትና እና ክርስቲያኖች እንደይነኩ ትዕዛዝ ወጣ፡፡ ሮማዊው አለም ግን ክርስትናን በመንግስት ሀይማኖት ደረጃ ለመቀበል ገና የቴዎዶሲየስን አዋጅ በ393 እ.ኤ.አ መጠበቅ ነበረበት፡፡ ክርስትና በሮሜ ስልጣኔ ውስጥ ስር በሰደደቸበት ወቅት ይኸውም በ6ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ዲዮናሲዮስ ኤክሲጂስ የተሰኘ ጳጳስ ተነስቶ ከዛሬ ጀምሮ በክርስቲያናዊው ዘመን አቆጣጠር መቁጠር አለብን በማለት አዲስ መንፈሳዊ አዋጅን አወጀ በዚህም ምክንያት ለ500 አመታት አንድ ቀን እንኳን ወደ ኋላ መለስ ብለው ስለ ጌታ ልደት ስለ ዘመነ ፍዳ ህልፈት እና የዘመነ ምህረት መስጠት አስበው የማያውቁት የሮሜ ቄሳሮች የድሮውን የዩልዮስ ዘመን አቆጣጠር ክርሲቲያናዊ ለማስመሰል ተሯሯጡ፡፡

ዲዮናስዮስም በግሌ ባጠናሁት ምርምር መሰረት ክርስቶስ የተወለደው ከሮሜ ጥንታዊ ግንባታ ተነስቶ ሲቆጠር 753ኛው አመት ላይ ነው ሲል ያመጣውን ስሌት እንዲሁ ተቀብለው በዩልዮስ ዘመን አቆጣጠር ላይ በመለጠፍ ወደ ፊት ተጓዙ፡፡ ውሎ ሲያድር ግን ኮከብ ቆጣሪዎቻቸውን የዘመኑን ቀንና የወቅቱን ነገር አጢነው ከምድር ወገብ አመት /12 ስአት ብርሃን እና 12 ሰአት ሌሊት/ ይረዝም የነበረው ማለትም 365.242197 ቀናት ጋር የማይስተካከልና ቅድሚያ ያለው የዩልዮስ ዘመን መቁጠሪያ መሆኑን አስገንዝበው በእነርሱ

ስሌት መሠረት የ11 ደቂቃና 14 «ሰኮንድ» ቅድሚያ በየአመቱ ተደማምሮ በ1000 አመት ውስጥ 7 ቀናት ሊደርስ እንደሚችልም አሳዮ።

ይህንን ችግር ለመቅረፍ ፓፓ ግሪጐሪ አስራ ስምንተኛ ክስቶፌር ካልቪነስ (1537-1612) የተሰኘ ኮከብ ቆጣሪውን በመያዝ በ1583 ስብሰባ አድርጐ በዘመናት እየተንከባለሉ የመጡትን አስር ትርፍ ቀናት በአንድ ለሊት ውስጥ ለማጥፋት ወሰነ ይህንንም ጥቅምት 5 ይውል የነበረውን በማግስቱ ይከበር የነበረውን «የቅዱስ ፍራንሲስ» በአል ሰው ከእንቅልፉ ሲነቃ በአዋጅ «ዛሬ ጥቅምት 15 ሆኖአል» ተብሎ በዚህም አስር ቀን እንዲወድቅ አደረጉ ማለት ነው። ይህ የተሃድሶ አካሄድ የጐርጐሪዮስ ዘመን አቆጣጠር በሚል አዲስ ሰያሜ ስለታወቀ በፊት የዩልዮስ ከዚያም «ክርስቲያናዊ» ቀጥሎም ዛሬ በመሻሻል ሂደት «ግሪጎሪያን ካላንደር» የተሰኘ ውን ዘመን መቁጠሪያ ሊጠቀሙ በቁ።

ምዕራባውያኑ እንደለመዱት ዛሬም «የግሪጎሪያን» ዘመን መቁጠሪያ ችግር የሞላበት ነው።» ማለታቸውንም አሳቋረጡም በአሁኑ ጥናት መሠረት የጐርጐሪዮስ ዘመን አቆጣጠር እንደ ፍራሽ አሁንም ታድሶ ወደ አለም አቀፋዊ ዘመን አቆጣጠር መምጣት አለበት ይሉናል ይህም በሁለት መንገድ የተዘጋጀ ነው የመጀመሪያው አለም አቀፋዊ (International calendar) የተሰኘው ዘመን መቁጠሪያ 13 ወሮች



ያሉትና በ28፣31 እና 30 የሚዋኙቁት ወሮች ሁሉ 28 በማድረግ አንድ ወጥ የሚያደርግ ሲሆን፣ የአለም (World calendar) የተሰኘው ዘመን መቁጠሪያ ደግሞ አንድ አመትን በአራት ወቅት የሚከፍልና እያንዳንዱ ወቅት 91 ቀናት ብቻ ያሉት ሲሆን አንድ ትርፍ ቀን የመጀመሪያው ወቅት ላይ የምትደመር ያለው ያደርገዋል ይላሉ።

ይህ አሰራር ከተዘጋጀ የቆየ ቢሆንም /20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነው/ ዛሬ ድረስ በተግባር አልዋለም። ምክንያቱ ደግሞ ለዘመናት እንደፈለጉ ሲያድሱትና የተለያየ ስም ሲሰጡት የነበረውን ዘመን መቁጠሪያቸው ይህን የመሰለ ለውጥ ቢያመጡበት ያለፈውን አቆጣጠር የሚያዛባና የሚያደናግር ስለሚያደርገው ወደ ስራ ይዘውት እንዳይገቡ ፍርሃቱ እንደ ቆፈን ወጥሮ ይዞአቸዋል። ታዲያ «የራሷ ሲያርባት የሰው ታማስል» እንደተባለችው የመንደር ሴት በብዙ ችግር ተተብትቦ በጓዳቸው ባለው የዘመን መቁጠሪያ ላይ ብቻ አተኩረው መስራት ሲገባቸው ስለኢትዮጵያዊው ዘመን አቆጣጠር ማን አስተያየት ስጡ አላቸው? ይሄ ደግሞ ከፍርሀት ለመላቀቅና የአለምን ተቀባይነት ለማግኘት ወደ እውነትና ስህተትን ማመን መምጣት እንዳለባቸው ያሳያል። እንዲሁም ለሰው ልጆች ፍቅር ኖሯቸው ወደ ሰላም መድረስ እንዳለባቸው ባለመረዳትና ባለመፈለግ የመጣባቸው ችግርን

የሚያሳይ ነው:: መፅሀፍ ቅዱስ «ፍቅር የፍርሃትን መንፈስ ያጠፋል» አይደል የሚለው! (1ኛ ዩሐ 4:18)



# ምእራፍ ስምንት

## *የጌታችን የመድሐኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደትና የሄሮድስ መንግስት*

በመፅሀፍ ቅዱስ ውስጥ በተደጋጋሚ እንደተገለፀው ጌታችን ሲወለድ ሄሮድስ ገሊላን እና ይሁዳን ጨምሮ ትራኮኒታስ፣ ቢታንያ እና የሃራንን አውራጃዎች ይገዛ ነበር:: ይህ ሄሮድስ በጌታ በሥቅለት ጊዜ ገሊላን ከገዛው ከልጁ ከሄሮድስ አንቲጳ የተለየ ነው ስሙም ሄሮድስ ወልደ ሐንጴፌር (አንቲጳተር) (Herod Antipater) በመባል ይታወቃል (ማቴ2:1:2) (የሉቃ 3:1) (ሉቃ 3:19) የገሊላን አውራጃም ከይሁዳ ጨምሮ እንዲገዛ በሮሜ ነገስታት በኦክቴቪያንና፡አንቶኒ የተወደደ ስለነበረ ተፈቅዶለታል::

በታሪክ እንደተዘገበው ይኸኛው ሄሮድስ የሮሜ ስራዊት የይሁዳ ወይም ምድረ እስራኤልን በቅኝ እንድትገዛ ወሳኝ የሆነ እርዳታን በፓርቲያውያን ጦርነት ጊዜ በማድረጉ ለዚህ ሥልጣን እንደበቃ ይታወቃል:: ‹ሄሮድስ ታላቁም› በመባል እንዲሞካሽም ምክንያት ሆነውለታል:: ይህ ሰው የቤተልሔምን 144,000 ህፃናትን ብቻ ሳይሆን የስልጣኔ ባለንጣ ናቸው ያላቸውን የራሱን ሚስት እና ልጅ (ማርያሚን

እና አንቲጳተር) ያስገደለ ነበር። በማቴዎስ ወንጌል በማቴ 2 ቁጥር 1-2 እንደተፃፈው ጌታችን ሄሮድስ በሚያስተዳድርበት ዘመን መወለዱን እንረዳለን ይህንንም መንፈሳዊ ጉዳይ ሄሮድስ ሊረዳ የቻለው በሰብአ ሰገል መምጣት ምክንያት ነበር ::[1]

ይህንን በጥልቀት የሚገልፀው መፅሀፍ ተአምረ ኢየሱስ ነው። በተአምረ ኢየሱስ ላይ ስለ ሰብዓ ሰገል ስለ ሄሮድስ እና ስለድንጋጤው ስለ ወስደው እርምጃ አንድ በአንድ ይዘረዝራልና ማየቱ ይበጃል ::

ለምሳሌ በተአምረ ኢየሱስ 7ኛ ተአምር ገፅ 28 እንዲህ የሚል ገፀ ንባብ አለ ቁጥርም11 ላይ ጀምረን ስናነብ «በኮከቡም ላይ እንደ ፀሀይ የሚያበራ ልጅዋን ታቅፋ ድንግል በብርሃን ዙፋን ተቀምጣ ትታያለች በልጅዋም እራስ ላይ የጌትነትን ዘውድ ተቀዳጅቶ ይታያል ይህ በታየ ጊዜ ሕፃኑ የተወለደበትን ቦታ ፈልጋቸሁ ማግኘት ይገባችኋል። ይህ ልዩ ኮከብ ስለ እርሱ በሰማይ ላይ ታይቷልና።» ሲል የሰብአ ሰገል አመጣጥን ያወሳል።

---

1-See the source professor Shmuel Safari, **The History of Israel from ancient times to the modern formation** (Jerusalem, 1973) pp.114-118



ከቁጥር 12 ላይ «አስቀድሞ አባታችን አዳም ከገነት ወጥቶ ከተቀመጠበት ከደብረ ቅዱስ ተገኝቶ አባቶቻችን ያስቀመጡት ወርቅና ከርቤ ስለ ጌትነቱ ክብር እጅ መንሻ አቅርቡለት የሚል ፀሑፍ አገኙ»

ከቁጥር 13 «ከዚህም በኋላ ሶስቱ ነገሥታት ሕፃኑ የተወለደበትን ቦታ ለማግኘት ምድርን ይዞሩ ዘንድ ቆርጠው ተነሱ ከነርሱም ጋር ሶስት መቶ ጭፍራ አስከትለው ወረቅና ከርቤውን ይዘው ኮከብ እየመራቸው ከምሥራቅ በኩል መጡ።»

ከቁጥር 14 «በጉዞአቸውም ጊዜ ብዙ ችግርና ፈተና ደረሰባቸው አገራቸው እጅግ እሩቅ ነበርና ኢየሩሳሌም እስኪደርሱ ሁለት አመት ፈጀባቸው »

ስምንተኛው ምዕራፍ ላይ ያለው ተአምር ደግሞ እንዲህ ይላል «ስለ ጌታ ኢየሱስ መወለድ የምሥራቅ ነገሥታትም ማለትም ሰብአ ሰገል ከብዙ ሠራዊታቸው ጋር ከሩቅ ሀገር ወደ አየሩሳሌም በመጡ ጊዜ የሀገሪቱ ሰዎች ስለሰዎቹ ሁናቴ ፍርሃት ያዛቸው።»

ቁጥር 3 «በዚያን ዘመን በኢየሩሳሌም የነገሰው ሄሮድስ ነበርና ሰዎቹን ከመፍራት የተነሳ ከብዙ ገፀ በረከት እና እጅ መንሻ ጋር ወደ ፋርስ ነገሥታት መልክተኞች ላከ።»

ቁጥር 4 «መልክተኞቹም ለፋርስ ነገሥታት እጅ መንሻውን አድርሰው ወደ ፍልስጤም ምድር በምን ምክንያት እንደመጡ ጠየቋቸው።»
ከገፅ 33 ላይ «ነገሥታቱም ለተወለደው አምላክ እጅ መንሻ ካቀረቡለት ከሰገዱለትም በኋላ ወደ ሀገራቸው ለመሄድ ሲነሱ አምለክን የወለደች በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ የፀናች ክብርት እመቤታችን የገበስ ዳቦ ስንቅ አሲያዘቻቸው ሌላ ምንም ነገር የላትም ነበርና።» እያለ ስለታሪኩ ይገልጥልናል።

በዚህ ሁሉ የምንረዳው ጌታ የሚወለድበት ሰአት በቀረበ ጊዜ ሰብአ ሰገል ከሀገራቸው መነሳታቸው እና በእግዚአብሔር መልአክ እየተመሩ ቤተልሔም በመድረሳቸው ሄሮድስ በፍርሃት መጨነቁን የሥልጣንም ጥመኛ ነበርና ከመንግስቴ ልወገድ ነውም ሲል በቤተልሔም ምድር ብቻ ያሉትን ህፃናት ማስወጨፍጨፉን እናይበታለን።ይህ በሆነ ጊዜ ጌታችን በእመቤታችን እቅፍ ሆኖ መስደዱን የሚገልጽ በመሆኑ ዋና ማስረጃ አድርገን ታሪኩን እንረዳበታለን። አንድምታ ወንጌል (Exigency) እንደሚያብራራው በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 2 ቁጥር 11 ላይ እንዲህ ይላል « [ሰብአ ሰገል] ምን ጊዜ ተነስተው ምን ጊዜ ደርሰዋል ቢሉ ለልደት ሁለት አመት



ሲቀረው ተነስተው የልደት ዕለት ደርሰዋል። ይህ በምን ይታወቃል ቢሉ ኤጲፋንዮስ 'ዮም ተወልደ' /ዛሬ ተወለደ/ ይላልና ሲሉ አበው ሚስጥራቱን ያጎሉበትን ክፍል እናያለን።

ሰብአ ሰገል ጌታ በተወለደበት ጊዜ የመድረሳቸው ሌላኛው ማነፃፀሪያና ማመሳከሪያ በጌታችን የስደት ወቅት መጥምቀ መለኮት ዩሐንስንም እናቱ ቅድስት ኤልሳቤጥ ይዛው አሸሽታው ነበርና ጌታና መጥምቀ መለኮትም የ6 ወር ያህል የእድሜ ልዩነት አላቸውና ጌታ የአርባ ቀን ሕፃን ሲሆን መጥምቀ መለኮት 6 ወር ሲሆነው ስደት ተጀምሮአል። በዚህም በበርሃ በነበረ ጊዜ እናቱ የምተቸበትን መጥምቀ መለኮት ዮሐንስን ጌታ ሚዳቆ እናት ትሆነው ዘንድ በበረሃም ሲኖር አንዲት ድንጋይ ቤቱ ትሆነው ዘንድ በታአምራት እንዳደረገለት በሚገልፀው የቤተ ክርስቲያን መፀሀፍ መመልከት ይበልጥ ስለ ነገሩ እውቀት ያስጨብጣል።

ስለ ዮሐንስ በሚገልፀው በገድሉ ላይ 7 አመት ከመንፈቅ ሲሆን እናቱ ኤልሳቤጥ ሞተች ይላል። ተአምረ ማርያምም እንዲሁ በስንክሳር ደግሞ ኤልሳቤጥ የሞተችው 7 አመት በበረሃ ውስጥ ከዮሐንስ ጋር ኖራ ነው (ዘመስከረም) ልዩነቱም 6 ወር ነው በዚህም ስደት የተጀመረው ጌታ ከ40 ቀን


መስዋእት ርግብ ከቀረበለት በኋላ ሲሆን ዮሐንስ 6 ወር ያደረገ ህፃን በነበረበት ጊዜ ነው የሚል ማመልከቻ አለው

በተአምረ ማርያም ወይም ከቅዳሴ ማርያም ውዳሴ ማርያም ትርጓሜ ከቁጥር 166 ገፅም 235 እንደምንረዳው ጌታችን በስደት ጊዜ በነበረ ጊዜ እመቤታችን ስለ ልጅዋ ጥምና ድካም የትዕማን ቤት ሄዳ ለመነች:: በዚያም የነበረችው እመቤቲቱ ፀባይሽ መጥፎ ቢሆን እንጅ አንቺን የመሰለ ከመጋረጃም መች በወጣ ነበር ብላ በማፌዝዋ ዬሴፍ አረጋዊ ቢገስፃት ኮቴባ የተባለችው ወደል ባርያዋ እመቤቴን ደፍሮ የሚናገረውን ይህንን ፍየል ጠባቂ አሳየዋለሁ ብላ መጥታ ዬሴፍን በጥፊ ቃጥታ ከእመቤታችን እጅ ህፃኑን ነጥቃ ወደ መሬት አውርዳ ጥላው አስለቀሳዋለች በተአምራቱ ኮቴባን እና እመቤቲቱን ሊረዱዋቸው የወጡትንም ጎረቤቶቻቸውን ሁሉ ዝንጀሮ ስላደረጋቸው የገዛ ውሾቻቸው ከቤታቸው አባርረዋቸዋል::

ስለ እነ ኮቴባ ጠቅሶ ይህ ገፀ ንባብ የጌታን እድሜ 2 አመት ያደርገዋል በዚህም አንድምታውና ተአምረ ማርያም (150 እና 270) የጌታን የስደት እድሜ 2 አመት ያደርጉታል



የጌታ እድሜ በስደቱ ጊዜ 6 ወር ነበር የተባለበትና በተደጋጋሚ አፀንኦት የተሰጠው ክፍል ምንጭ መፀሀፈ ስንክሳር ሲሆን ከጌታ ልደት ታህሳስ 28/29 ጀምሮ እስከ ግንቦት 24 (እመቤታችን ልጅዋን ሄሮድስ እንዳይገድልባት ከዮሴፍና ከሰሎሜ ጋር ተሰዳ ግብጽ የገባችበት እለት) ያሉትን ወሮች በመቁጠር እንደሆነ ሰው ሊረዳ ይገባል:: ማንም ሰው ዘሬም ቢሆን የተወለደበትን ወር ይዘን እድሜው ይህን የህላል ብለን በሙሉ ቁጥር እንጠራለን እንጂ የተወለደው ታህሳስ 29 እድሜው 2 ወር ከሁለት ቀን በማለት የካቲት 30 ላይ ስላለ ህፃን አንናገርም ስለሆነም ከታህሳስ ጀምሮ እስከ ግንቦት ድረስ ስንቆጥር 6 ወሮችን እናገኛለን::




መግለጫ 3 :የጌታችን ከቤተልሔም ተነስቶ ግብፅ የሄደበት ስደት የወሰደው ጊዜ

ለነገር የተባ ሰው «ከታህሳስ 2 ቀን የያዘ ለግንቦት 6 ቀን የጉደለው ህፃን ነበር ጌታ በሰአቱ» ሊል ይችላል:: ወይም «5

ሙሉ ድፍን ወር ከ 26 ቀን አድርጓል» ሊልም ይችላል ምንም ቢሉ ምን ወደ 6 ወር ያደላ እንጂ ሌላ አይባልም::

እንደ ኢትዮጵያውያን የጥንት ባሕረ ሐሳብ የዘመን ዝርዝር (chronology) አመተ ምህረት የሚጀምረዉ የጌታ ልደት በሆነበት አመት መስከረም አንድ ዓ. ም ነው ስለዚህ 1ኛው አመተ ምህረት ታህሳስ 28 «ክርስቶስ ተወልደ» እንላለን:: ከዚያም 40 ቀን የኦሪት መስዋት ስዋ፤ ለ3 አመት ከ 6 ወር ስደት፤ በ4 አመቱ ወደ ምድረ እስራኤል መልስ ወይም ሞተ ሄሮድስ ሲል በ12 አመቱ ቤተ መቅደስ መግባቱን ሊቀ ከህናትን መጠየቁን እና ማስረዳቱን በ15 አመቱ ጢባርዬስ መንገሱን በ30 አመተ ምህረት ጥር 11 ጥምቀት በ34 ዓ.ም መጋቢት 27 ስቅለት ፤ በ317 ጉባኤ ኒቅያ ፤ በ 373 ጉባኤ ቁስጥንጥንያ፤በ423 ጉባኤ ኤፌሶን፤በ 444 ጉባኤ ቁልኬዶን (ከለባት) እያልን እንቆጥራለን::

ይህን ሁሉ ለማለት የተፈለገው ወደ አንድ ድምዳሜ ለመድረስ ነው:: ይኸውም ስለ ሄሮድስ ሞትና የአውሮፓውያኑ ዘመን መቁጠሪያ ሄሮድስ ሞተ የሚለው በ



4ኛው ቅ.ል.ክ (B.C) ስለ መሆኑ በደንብ እንድናጤን ተፈልጎ ነው::[1]


በወንጌል ደግሞ እንደምናነበው ሄሮድስ የቤተልሔምን ህፃናት ያስፈጀው ከሞተ በኋላ 4 አመት ቆይቶ ተነስቶ ሳይሆን አልቀረም ማለት ነው እንደ አውሮፓውያኑ ዘመን አቆጣጠር:: ይህ ከወንጌልና ከክርስቲያኑ ዘመን መቁጠሪያ ጋር የማይሄደው የምእራባውያን ዘመን አቆጣጠር እራሳቸው አምነውና መርምረው እያማጡ ጌታ የተወለደው በ6 ቅድመ ልደት ክርስቶስ ሳይሆን አይቀርም ብለዋል::[2]

---

1 Seven day Adventist Bible commentary (vol. 5) S.V Herods (review and herald publishing, 1956) p.42

2. -See the censes of Quirinius and the birth of Jesus of Nazareth, internet source.

ይህንንም ሲሉ ሄሮድስ የሞተው በ4 ቅ.ል.ክ ከሆነ እንደሁም የቤተክርስቲያ ህፃናትን ሲያስጨፈጭፍ ከ2 አመት በታች ያሉትን ግደሉ ካለ በኋላ ወዲያው ሞተ በማለት ወንጌልን እንኳን በቅጡ ለመረዳት ቸግሮአቸው በውል ሲዳክሩና ሲቃዡ ይስተዋላሉ:: እንደነርሱ አባባል የዘመን አቆጣጠሩ በዘመን መስመር ላይ ይህንን ይመስላል::




መግለጫ 4 :-የምእራባዊያኑ የዘመን አቆጣጠር ከጌታ ልደት ጋር ሲያነፃፀሩ

ስለዚህ ጌታ በ6 ቅድመ ልደት ወይም ዘመነ እግዚአ ሳይወለድ አልቀረም ይሉናል:: በነገራችን ላይ ግን ወንጌሉ ሄሮድስ የቤተልሔምን ህፃናት እንዳስገደለ ሞተ ይላልን? ጌታ ከስደት በተመለስ ጊዜ እድሜው ስንት ነበር? ለስደት ሲነሳስ እድሜው ስንት ነበር? የጌታ የስደት ዘመን የቤተልሄም ህፃናት ጭፍጨፋ በኋላ ለ2 አመት ነው ብሎ ለመደምደም በምን ማስረጃ ይችላሉ? በወንጌሉ ቃል (ማቴዎስ) ላይ እራሱ



ሄሮድስ ከሁለት አመት በታች የሚያህላቸውን ህፃናት ግደሉ ይላል እንጂ ሁለት አመት የሞላቸውን ህፃናት ብቻ አላለም ይህ ታዲያ ቅራኔ አልሆነባቸውም?

ከላይ ባየነው ሁናቴ ሄሮድስ ሞተ ብለው የሚናገሩትን አመት ያገኙት ከፍላቪየስ ጆሴፈስ ከተባለ የአይሁድ የታሪክ ፀሀፊ ስራ ሲሆን ጆሴፈስ ሄሮድስ የሞተው እንደጥንታውያኑ የሮማውያን አቆጣጠር ሮሜ ከተመሰረተች በ 750 አመት በኋላ ነው ሲል ያስቀመጠውን በመያዝ በሉቃስ ወንጌል ላይ ም1:3 :22-23 ላይ ጌታችን ስብከቱን ሲጀምር ጢባርዮስ ከነገሰ በአስራ አምስተኛይቱ አመት ነበር ሲል ገልፆ የጌታን እድሜ 30 በማድረጉ ይህንን ይዘው በመንደርደር ጢባርዮስ እንደ ጥንታውያኑ የሮሜ አቆጣጠር የነገሰው በ 765 ላይ ሲሆን አስራ አምስት አመት ተደምሮበት ወደ 780 ሲገባ ያም ላይ 30 አመት ሲቀነስ 750 ስለሚመጣ ዲዮናሲዮስ ኤክሲጆስ የጌታን እድሜ በጥናቱ ደረስኩበት ካለዉ ከ 753 (አንድ አመተ እግዚአ የሚቆጠረው 750 ጀምሮ እስከ 753) ላይ የአራት አመት ልዩነቶችን ያሳያል በሚል ነው::

በዚህም ጥንታውያኑ የሮሜዎች ዘመን አቆጣጠር አፈታት ላይ እራሱ ችግር እንደለ መረዳት ቀላል ነው እንዴት ነው የጌታ እድሜና የሄሮድስ ሞት የተገጣጠመው በማለት ጌታ ሲወለድ ሄሮድስ ሞተ ማለት አይሆንም ወይ ? የሚል ወሳኝ ጥያቄ መጋረጥ ያስችለናል ነገር ግን ዘመን አቆጣጠሩ የተዛባና በይበልጡኑ ደግሞ የጢባርዮስ የንግሥና ዘመን ያሳሳታቸው ስለመሆኑ ጥርጥር የለውም።

እንደ ቤተ ክርስቲያናችን እውነተኛና ቀና አፈታት ጌታችን በእመቤታችን ጀርባ ታዝሎ ወደ ግብፅ እና ኢትዮጵያ ሲሰደድ ስድስት ወሩ ነበር። በግብፅና በኢትዮጵያም እየተዘዋወሩ ምድሪቱን ባርከዋል። ከ3 አመት ከ6 ወር በኋላ ሔሮድስ ስለሞተ የጌታችን መላእክ ወደ እስራኤል ምድር ይመልሳቸው ዘንድ ተገልፆ ዮሴፍን አዘዘው (ማቴ 1:19-23)

የጌታ የልደት ዘመን 3 አመት ከ6 ወር ነው የሚባለው በዮሐንስ እራኢ 12: 13-16 ጀምሮ ያለውን ገፀ ንባብ ሚስጢር በአንድምታ በተፈታበት መሠረት መሆኑን ባለፉት ክፍሎች አይተናል። በዚህ ሁናቴ 6 ወር ከ3 አመት ከ6 ወር ላይ ሲደመር የጌታን እድሜ በሞተ ሄሮድስ ጊዜ ላይ




አራት አመት የደረገዋል በዚህ ላይ ሄሮድስ ሲሞት በአንድ ቀን ከጣና ደሴት ተነስተው ምድረ እስራኤል መግባት ቢቻላቸውም ለጌታ ተድላ ሥጋ የለበትምና (ለተከታዮቹ ስደትን ይባርክ ዘንድ አምላክ እራሱ የሥጋን ፈተና ይቀበላልና) ምድረ እስራኤል ድረስ በእግር ተጉዘዋል። የጌታን ሥደት ታሪክ እያብራራ የሚገልጸው ተአምረ ኢየሱስ ጌታ ከስደት መልስ ናዝሬት ሲገባ እድሜው 5 አመት መሆኑን ይገልፃል። ተአምረ ኢየሱስ አስራ አራተኛ ተአምር ገጽ 49 ጌታ ወፎችን ከጭቃ ፈጠረ የሚለውን ተመልከት

ከላይ ባየነው ድምር 'ሞተ ሄሮድስ' የጌታ እድሜ 4 አመት ሲሆን የመጣ መሆኑን እንረዳለን እንጠነቅቅማለን።

ምእራባውያኑ የሄሮድስን ሞት ካገኙበት ወይም አገኘነው ካሉት ከጆሴፈስ አይሁዳዊ ዘመን ጥቆማ በመነሳት እና መመርመር መልካም ነው።ያ ደግሞ የሄሮድስን ሞት በ4 ቅ.ል.ክ. ያደርግባቸዋል። ይሄ ደግሞ ለኛ ወሳኝ የሆነ መረጃችን ነው። በወንጌል እንደተፃፈውና አሁን አለሙ ሁሉ እንደሚስማማው ሔሮድስ ከጌታ ልደት በፊት የሞተ ሳይሆን ጌታ እድሜው 4 ዓመት ሲሆን የሞተ መሆኑን ከላይ እንዳየነው ተረጋግጦአል አቆጣጠሩንም ከላይ አይተነዋል።

ይህ ደግሞ ሲተነተን አውሮፓውያኑ አንድ አ.እ ወይም (Anno dominie) ብለው መቁጠር የጀመሩት ጌታ እድሜው ሰምንት አመቱ ሲሆን ነው ለማለት ያስችላቸዋል እነርሱም ይህንን መረጃ ይዘው በቅጡ ሳይመረምሩት ሊታበዩ ይፈልጋሉ ነገሩ ግን ከዚያ በጣም የተለየ መሆኑን እንመልከት:: ይህ በንፅፅር ሲታይ ይህን ይመስላል::




መግለጫ 5 :-ክርስቲያናዊውና ጎርጎሪያዊው ዘመን አቆጣጠር ልዩነት

ይህ ማለት ጌታችን ሄሮድስ እስኪሞት አራት አመት የነበረ ሲሆን ሄሮድስ ከሞተ በኋላ በጐርጐርያውያኑ ዘመን መቁጠሪያ አራት አመት ድረስ ቅድመ ልደት ክርስቶስ ሆኖ የሰነበተበት ዘመን አለ:: እነዚህን 4 ( የጌታ እድሜ ) 4 ሄሮድስ ከሞተ በኋላ ያለው ያልተቆጠረ አመት ሲደመሩ የ8 አመት ልዩነት ያመጣሉ::



እንደ ዲዮናሲዮስ ስህተታዊ ግምት ጌታ ተወልዶአል ሲል ያስቀመጠው አመት ከእውነተኛው ልደት በ8 አመት የቀደመ ሲሆን በ4 አመት ወደ ኋላ ቢያወርደው ሞተ ሄሮድስን እንደገና 4አመት ወደ ኋላ ቢያወርደው የጌታን ልደት ይደርስበት እንደነበረ ማወቅ ያስፈልጋል ዲዮናሲዮስ በ532 ዓ.እ ላይ የጌታ ልደት ከሆነ ዛሬ 532 አመት ነው ያለበት ጊዜ ላይ 8 አመት የግድ ሊቀነስ እንደሚገባው ከላይ አይተናል ስለሆነም እርሱም 532 ያለው አመት በእርግጥ 524 ነበር:: የ 8 አመቱ ጭማሪ ስህተት ተጠያቂ ዲዮናሲዮስ ሲሆን ባለማረም ያላስተካከሉት ደግሞ የአሁኑ ዘመን ምዕራባያውያን ናቸው::

ስመሆኑ ጌታ ከመወለዱ በፊት አራት አመት ሄሮድስ ሞቶ ነበር ብሎ የሚያሳያቸው ዘመን መቁጠሪያና ለዘመናት ስለ አቆጣጠራቸው አንድስ እንኳን በጥበብ ጉልህ ስህተቱን አለማሳየቱ አውሮፓውያኑ ለመፅሀፍ ቅዱስ ምን ያህል ዝቅተኛ ግምት እንደ ሚሰጡ እና የሚያወሩትንስ እንኳን እንዳላወቁ ያረጋግጣል::

ይህ ማለት ደግሞ ዛሬ ላይ በማስተዋል ስንመለከተው ጌታ ከተወለደ በኋላ እስከ 8 አመት ድረስ ያለውን ጊዜ አንዱ ብለው ሳይቆጥሩ ፈረንጆቹ ዘግይተው የተነሱ ናቸው:: በማለት አንዳንዶቹ የነሱ ዘመን መቀጠሪያ ላይ 8 ዓመት የኛ ላይ 16 አመት መደመር አለበት ይላሉ:: ሀሰቡ ግን እጅግ ስህተተኛ

ነው:: ምክንያቱም እኛ ስንቆጥር ሄሮድስ ከጌታ ልደት በፊት ሞቶአል አላልንምና በዚህም ስሌት ይህችን ስምንት አመት ስንመለከት የአፊ ታሪኩን የሮሜ ግንባታ አቆጣጠር እና የዲዮናስዮስ ስሌት ምን ያህል የተሳሳቱ መሆናቸውን እንረዳለን ስለ ሆነም የኛ ዘመን 2000 ሲል የፈረንጆች 2008 በማለት ይህቸን የ8 አመት ልዩነት በግልጽ ወጥታ ስትመጣ እንመለከታታለን የእኛ ዘመን አቆጣጠር በማስረጃ ሲታይ ይህን ይመስላል::




ማመልከቻ 6:- ክርስቲያናዊው የዘመን መስመር በጌታ እድሜ

ከላይ ያየነው የ7 አመት እና የ15 አመት ጭፍን መደመር የነጮችን (የጕርጕሪዮስና የዲዮናስዮስና ድርሰት አፊ ታሪካዊው የሮሜ ግንባታ ወደ ኋላ የሚቆጥር በማስመሰል) ትክክለኛ አመዘጋገብና ስህተት የሌለው የአመታት ምዝገባ ነው ከሚል መደምደሚያ የሚነሳ በመሆኑ በራሱ ውድቅ ሃሳብ እንዲሆን የደርገዋል ይህንንም በዝርዝር ቀጥሎ እናየዋለን::

ለክርስትናው ሃይማኖትና ባህል በጣም ቅርብ ትስስር ያለው የግብፅና የኢትዮጵያ ህዝብ ስለ ጌታ ልደት አመታቱን ከአሪት ጋር እያጣመሩ ለመቁጠር ይቀድሙ እንጂ አያንሱም ስለዚህ መላ የሌለውን የህፃናት ተረት ላይ የተመሰረተ




የዘመን መነሻ አድርገው ከሚቆጥሩ የዘመን መቁጠሪያዎች ይልቅ የኛው ዘመን መቁጠሪያ ስለሚበልጥ ነገሩን በጥንቃቄ መርምሮ 8 አመት ከምዕራባውያኑ ማንሳት የግድ ይላል:: ይህ ማለት ደግሞ ከምራባውያኑ 2008 ላይ 8 አመት ሲቀነስ 2000 ዓ.ም ይሰጠናል:: ይህንን በይበልጥ የሚያጠናክር መረጃ በሚቀጥለው ምእራፍ እናያለን::

ከዚህ ላይ ግን በአስተውሎ ሊመረመሩ የሚገቡ ብዙ የተወዛገቡና የተሳከሩ ታሪኮች እና የመፅሀፍ ቅዱስን መረጃ የማያስታርቁ አመቶች በምዕራባውያን አቆጣጠር ዘንድ አሉ:: እነዚህም፤

1ኛ በሉቃስ ወንጌል 3:22 ላይ ያለው የጌታችን መጠመቅና እድሜው ሰላሳ አመት ሲሆን ጢባሪዮስ ከነገስ 15ተኛይቱ አመት የመሆንዋ ጉዳይ

2ኛ በጥንታዊው የሮሜ አቆጣጠር መሠረት ጢባረዮስ በ765 ነግሶአል ስለሚባለው አቆጣጠር

3ኛ ሄሮድስ በ750 አመት ነው የሞተው የሚለውን ጥንታዊው የሮሜ አቆጣጠር ከግሪጐሪያውያኑ ጋር እንደገና: ሲመሳከር የሚያሳዩት ይህ ነው የማይባል ግራ የተጋባ እና የተመሳቀለ ልዩነት ነው:: በመጀመሪያ ነጥብ ብንጀምር በዘመን መሰመር ላይ ሀሳቡ ሲቀመጥ ይህንን ይመስላል::




ማመልከቻ 7:- አመተ እግዚእ እና ጥንታዊው የሮሜ አቆጣጠር ሲመሳከር


ከላይ እንዳየነው በአሁኑ ሰአት ጌታችን ከ4 እስከ 6 አመት በፊት ተወልዶአል ወደሚል ድምዳሜ ላይ ተደርሷል:: የሄሮድስ ሞት 750 ላይ የመሆን ምክንያት ወደ እዚህ ድምደሜ መድረሳቸው ዋና ምክንያት መሆኑም ይታወቃል:: በዚህ ስሌት መሠረትም 750 እስከ 780 ሰላሳ ዓመት እንደሚሆን መመልከት አያዳግትም ብሎም የጢባርዬስ ንግስናን 765 ከሆነ ደግሞ አስራ አምስት አመት እላዩ ላይ ሲጨመሩ 780 የመምጣቱንም ነገር ማወቅ ቀላል ነው:: ይህ ግን ከአመተ እግዚእ (AD) አቆጣጠር ጋር ሲቀመጥ ጭራሹኑ እየተሳከረ የሚሄድ መሆኑን መገንዘብ ይገባል በተለየኛም ሁለተኛውንም ነጥብ የሚነካ ስለሆነ አብሮ መተንተን ተገቢ ነው::

ጢባርዮስ በታሪክ አመዘጋገብ ነገስ ተብሎ የሚታወቀው በ14 አመተ እግዚእ ስለሆነ በቀጥታ በሮሜ አቆጣጠር በ766 ዓመት በመሆን ይተረጐማል ይህ ማለት ደግሞ ከ766 ላይ 15 ሲደምሩ 781 እንጂ ሌላ ቁጥር አይሰጥም በአጭሩ ለመናገር የጌታን ልደት በ750 (በሞተ



ሄሮድስ ዘመን ነው) ካልን የጢባሪዮስን ዘመነ ንግስና 766 ነው ካልን የጌታ እድሜ 31 በጥምቀቱ ጊዜ ልናደርገው ነው:: ይህ ደግሞ ወንጌሉን የሚቃረን ስለ ሆነ ስህተቱ ያለው በጢባርዬስ የንግስና ዘመን መሆኑን ብዙዎቹ ወደ ማመን ይመጣሉ:: ይህንንም የሚያብራሩበት መንገድ አለ:: እኒህም ሰዎች ጢባሪዮስ ከ13 አመተ እግዚእ ጀምሮ እንደገዛና ሙሉ ባለ ስልጣን በመሆኑ የንግስናው ዘመኑ አስራ አራት ይባል እንጂ በአስራ አራት አ.እ የአውጉጦስ ሞት በመሆኑ እንዳሁ በቀድሞው ስልጣኑ ቀጥሉብትል ይህ አስራ አራት አመተ እግዚእ ስለዚህ የሚዘግበው የአወግስጦስን ሞት እንጂ የጢባሪዮስ ንግስና በ13 አመተ እግዚአ ነው የሚል ሃሳብ ነው:: ነገር ግን በዚሁ ሀሳብ ላይ ደግሞ ብዙ ስህተቶች አሉ:: እነኝህም የሚከተሉት ማመሳከሪያዎች ናቸው::

ጢባሪዮስ በነገሰ በ15ኛይቱ አመት ጌታችን እድሜው ሰላሳ ከነበረ ጢባሪዮስ ሲነግስ ጌታ እድሜው እኩሉን ወይም 15 አመት ነበር ማለት ነው:: ይህ ደግሞ ከ765 ላይ ሲቀነስ (15 አመት) ወደ 750 ያመጣናል:: ይህ ደግሞ ጌታ ሲወለድ ሄሮድስ ሞተ ማለት ነው:: ቅድም በዘመነ እግዚእ ላይ ጢባሪዮስ በ13 ቢሉ በ14 አመተ እግዚእ ነገሰ የሚለው ላይ የግድ 4 አመት ጨምሮ ከ753 የተነሳውን የዲዮናስዮስ አቆጣጠር ወደ 750 መመለስ መደመር ግድ ይላል:: ሊደረግም በዘመን መስመር ላይ ይህንን ይመስላል::





ማመልከቻ 8: የጥ.ሮ.አ ከአመተ እግዚአ ጋር ከጌታ ልደት ካሉት ዘመን ሲነሳ (ድ.ል.ክ.ማለት ድህረ ልደተ ክርስቶስ)

በዚህም (ሞተ ሄሮድስ) ወይም የጌታ ልደት 750 የተባለው ተፍልሶ 751 ይሆናል:: የለም 750 የተወለደበት ስለሆነ አንድ ብለህ ቁጠር ለሚል ደግሞ የጢባሪዮስ ንግስና በ764 ጥንታዊ የሮሜ አቆጣጠር (ጥ.ሮ.አ) ላይ ይመጣል:: ይህ ደግሞ የጢባርዮስ ዘመነ ንግስና የተባለው ጋር ችግር እንዳለበት አመላካች ነው:: ምክንያቱም (ከሙሉ ቁጥር 750 ጀምሮ እስከ 759) በየትም ዘመን አቆጣጠር ላይ ተነስቶ ሲቆጠር አስር አመት መሆኑን ከመረዳት ጋር ተያይዞ ጌታ በ 750 ጥ.ሮ.አ ከተወለደ 750 አንድ አመት ተብሎ የሚጠራ በመሆኑ ነው:: ይሄ ደግሞ የጌታን እድሜ በ15 አመቱ ላይ በጥንታዊው የሮሜ አቆጣጠር ወደ 764 ያመጣዋል::

በመጨረሻም እነዚህን አቆጣጠሮች ማለትም በ750 የጌታ ልደት ነው ብሎ በሚያስበው ጥንታዊው የሮሜ አቆጣጠርና ዘመነ እግዚአ ወይም ጐርጎሪያዊው ዘመን አቆጣጠር በዘመን መሰመር ላይ አብረው በተነፃፃሪ ሁኔታ ሲቀመጡ ይህን ይመስላሉ






ማመልከቻ 9:- ሶስቱ የጌታን ልደት ዘመን ከተለያዩ አቆጣጠሮች ጋር እንዲሁም የታሪክ ማመላከቻዎች ጋር የሚያሳይ

ከዚህ ጋር በግልፅ የሚታየው የምንገነዘበው ነጥብ ቢኖር የምእራባውያኑ ዘመን አቆጣጠር እርስ በእርሱ የሚጋጭ በመሆኑ ምንም አመኔታ ሊቸረው እንደማይችል እርስ በእርሱ ሲመሳከር በግልጥ ይታያል:: በተዘማጅ ደግሞ የኢትዮጵያው ዘመን አቆጣጠር ትክክለኛ ነው ሲባል በዚህ ውስን ማስረጃ ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ጠንካራ መረጃዎች ጭምር የተደገፎ ስለሆነ በሚቀናለው ምእራፍ ይህንኑ እናያለን::

እዚህ ላይ ለማከል ያህል የዮልዮስ ዘመን መቁጠሪያ እንደ ጎርጎሪያውያኑ በ42 ቅ.ል.ክ. አንድ ብሎ የተጀመረ ነው የሚለውን ይዘን ዲዮናሲዮስ በ532 አ.እ ላይ የጌታ ልደት አመት ብሎ ያስተማረውን ትምህርት የቆጠረበት የትኛው እንደሆነ ማለትም በጥንታዊ ሮሜ ይሁን በዩልዮስ ወይም በዲዮናሲዮስ አንድ እያሉ የቆጠሩበትና የሚያመሳክሩበት ዘመን መቁጠሪያና ዘመን አቆጣጠር በይበልጥ ውሉ የጠፋ ባሕረ ሐሳብ እንዲኖራቸው ምክንያት ሆኖአል ዩልዮስ አንድ አመት ብሎ የቆጠረውን ዛሬ ላይ ለማግኘት ብሎም በዚያ ሲቆጥሩ የነበሩትን (ጥ.ሮ.አ) ምእተ አመታት በመያዝ እስከ ዲዮናሲዮስ ደርሶ እርሱ ዩልዮናዊውን ወይም ጥንታዊውን ሮሜ ዘመን መቁጠሪያን ለታሪክ አካሄድና ለምርምሩ የትኛውን እንደያዘ ለመረዳትና ለማወቅ በጣም ይቸግራል:: በእውነትም ግራ ያጋባል!

ይህንንም አመት እስካላወቁ ድረስ ብሎም የጥንታዊ ሮሜ አቆጣጠር ቀርቶ ዩልዮስ የተካው እና የተሰራበትን ዘመን ካልተረዳን ወደ ድምዳሜና ግልፅ አቆጣጠር መምጣት አይቻልም::

እንደ አንድምታ ወንጌል ዘሉቃስ ም3 ቁጥር 1-2 ሌላ ልዩ የሆነ የጌታ ልደት ማመልከቻ ተቀምጦአል ይኸውም እንደ አቡሻከር አጉስጦስ (ኢክቴቪያን) በነገሰ በ42ኛው አመት ጌታ ተወለደ ሲል የአውግሰጦሰ ንግስና በ43/42 የነበረው




ሁለተኛው ትሪውምቪራ (ሶስትዮሽ ግዛት) የሚጠቀም ይመስላል ከዚህ አቆጣጠር ጋር አያይዞ አውግስጦስ ንጉሰ ነገስትነቱን ደርቦ በያዘ ጊዜ ማለትም ተቀናቃኝ ወይም ግዛት ከፍሎ የሚገዛ እንደ ማርክ አንቷን ያለው በጠፋለት ጊዜ ይህም በ27 ቅ.ል.ክ ላይ አስራ ስምንት አመት ሲደምሩ (ሲቆጥሩ) የጌታ ልደት አመት ነው ይላል




ማመልከቻ 10:- ከላይ የተጠቀሰው ዘመን ከጎርጎርዮስ አቆጣጠር ጋር ሲነፃፀር


ከ26 ቅ.ል.ክ ላይ 18 አመት ሲቀንሱ (ቅ.ል.ክ ስለሚቀንስ) 8 ቅ.ል.ክ ትመጣለች (ይህችን የስምንት አመት መዘግየት ተመልከት) ነገር ግን ይህ ምልከታ 8 አመት ከምእራባዊው አቆጣጠር የተለየ ሆኖ ሲያሳየን ወደ ኋላ የዘገየበት የራሱ የሆነ ምስጢር ያለው በመሆኑ ወደ አንድ ድምዳሜ ለመድረስ አስቸግሮአል:: እንደ ሄሮድስ ሞት ወደ ኋላ 8 አመት የሚያመለክት ይሆንን? በእርግጥም ከላይ ያየናቸው ሁሉ ይህንን የሚያወሱ ከሆነ ይህም ተመሳሳይ የሆነ ትርጓሜ ያለው ይመስላል ነገሩን ግን በጥልቅ በመመርመር አቡነ ቄርሎስ ይህን ያሉበትን ምስጢር በደንብ ማጥናት ይጠይቃል::

ይህ ማመልከቻ በዘመን መስመር ሲቀመጥ የሚከተለውን ይመስላል





ማመልከቻ11:- ጠቅላላ የአንድምታው የጌታ ልደት ማመልከቻ

በአንድምታው ላይ በንፅፅር የተቀመጡ ሶስት ማመልከቻዎች አሉ:: እነሆም የመጀመሪያው በሉቃስ ወንጌል ላይ ያለው ጌታ በጥምቀቱ ዘመን 30 ሲሞላው ዮሐንስ መጥምቅ ዘመኑ 30 አመት ከመንፈቅ ሲሆን ያለው ጋር አያይዞ ጢባሪዮስ በነገሰ በ15ኛይቱ አመት የምትለውን ይዞ «ጌታ ከአውጉስጦስ ዘመነ ንግስና 15 አመት ከጢባሪዮስ ዘመነ ንግስና 15 አመት ያመጣል::» ይላል ይህም በዘመን መስመር ሲታይ ይህን ይመስላል







ምእራባውያኑ ጢባርዮስን በ14 አ.እ ነገሰ ሲሉ አውጉስጦስ በ 14 አ.እ ሞተ ይላሉ ሁለተኛው ማመልከቻ የአውጉስጦስ ዘመነ ንግስና በጠቅላላው 56 አመት ነው ከዚያም ዘመን ውስጥ እርሱ (አውጉስጦስ) በነገሰ በ42ኛይቱ አመት ላይ ጌታ ተወለደ የሚል ነው:: ይህም 41 አመት ሲሆን እርሱ ከነገሰ በኋላ ያለውን አንድ ሁለት፣ እያሉ ሲቆጥሩ ይገኛል ማለት ነው::





ማመልከቻ12:- አውጉስጦስ የገዛበት ዘመን ከጌታ ልደት ጋር ማነፃፀሪያ

ሶስተኛው ማነፃፀሪያ ቅዱስ ቄርሎስ የተናገረው ሲሆን እርሱም ብፁእ ቅዱስ የሆነ የክርስትናን ሀይማኖት ጠባቂ የተዋህዶ አርበኛ የትሩፋትና የገድል መምህር ሊቀጳጳስ ዘ እስክንድርያ ነው:: አቡነ ቄርሎስ እንዳስተማረው አውጉስጦስ ንጉስ ነገስት ከተባለ በኋላ አስራ ስምንት አመት (ይህም ንጉስ ነገስት የተባለበት አመት ተቆጥሮ ነው) ሲቆጥሩ የሚያገኙት ነው ይላል በዘመን መስመር ላይ ይህ ሲቀመጥ ይህንን ይመስላል




ማመልከቻ13፡- የቅዱስ ቄርሎስ ማመልከቻ

ምእራባውያን በ42 ቅ.ል.ክ አውጉስጦስ ትሪውምቪራ በሚል ሶስትዮሽ ከማርክ አንቷንና ጋር ነገሰ ሲሉ በ27 ቅ.ል.ክ ላይ ደግሞ ተቀናቃኞቹ ጠፍተው ንጉስ ነገስት ወይም አምባገነን ተባለ በማለት የሚቀጥለውን ዘመን መስመር ያስቀምጣሉ፡፡




ማመልከቻ14፡- የግሪጎርያን አቆጣጠርና የአውጉስጦስ ህይወት

በዚህ አዲስ ማመልከቻ ከጎርጎርያውያኑ ጋር ያለው ልዩነትን በአግባቡ ለመረዳት አቡሻከርንና የቅዱስ ቄርሎስን ድርሰት በሚገባ ማጥናት ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም ለወደፊት ምርምር እንዲደረግበት የማመለከት ሥራን ይህ ፅሁፍ በማሳየት ለወደፊት የምርምር መንደርደሪያ ሊሆን ይችላል፡፡



# ምዕራፍ ዘጠኝ

## የቅዱስ ሉቃስ ወንጌል ታሪካዊ ማመልከቻና አይሁዳዊው

## ጆሴፈስ የፃፈው የአይሁድ ታሪክ

በመፀሀፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ጌታችን ልደት በጥልቀት ከፃፉት መካከል ቅዱስ ማቴዎስና ቅዱስ ሉቃስ ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ቅዱስ ሉቃስ በወንጌሉ ምዕራፍ 2 ቁጥር 1 ጀምሮ እንደተፃፈው «በሮሜ አውግስጦስ ቄሳር ነግሶ ሳለ በሶሪያ ቄሬኔዎስ ደጃዝማቹ (ገዢ) በተባለበት ጊዜ ከቄሳር ትዕዛዝ ወጣ ይህም የእስራኤል ሰው ሁሉ ይቆጠር ዘንድ የሚያዝ ነበር፡፡» ይላል በዚህ ገፀ ንባብ ዋና ተጠቃሽ የታሪክ ማመላከቻ ቄሬኔዎስ በሶሪያ ደጃዝማች በሆነ ጊዜ የሚለውና ከቄሳር ሰው ሁሉ ይቆጠር (ይፃፍ) ዘንድ ትዕዛዝ ወጣ፡፡ ይህችም የመጀመሪያይቱ መቆጠር (መፃፍ) ናት የሚሉት ሀረጎች ናቸው፡፡

ጆሴፈስ የሚባል በ32? [1] አመተ እግዚእ እስከ 100 አመተ እግዚእ እንደኖረ የሚነገር አይሁዳዊ ሰው ነው፡፡

1. የጥያቄ ምልክት መኖሩ የምእረባውያኑን አቆጣጠር ስህተተኛነት የሚያሳይ መሆኑን እና አመታቱ በትክክል የተመዘገቡ እንደይደሉ ያመለክታል

ይህ ሰው በመጀመሪያው አመተ ምህረት ላይ ስለነበረው ሁናቴ፣ ስለ አይሁድ ጠቅላላ ታሪክ፣ ብሎም ስለ ጌታችን፣ ስለ የመጀመሪያው ህዝብ ቆጠራ እና ስለ ሄሮድስ ሞት የዘገበ የታሪክ ፀሀፊ ነበር::

ጆሴፈስ በ70? አመተ እግዚእ የእስራኤላውያን አመጽ እና የእየሩሳሌም ጥፋት ውስጥ መሪ ሆኖ የተሳተፈም ጭምር ነበር፡ በዮዳፋት የነበረው ምሽግ ውስጥ የነበሩት አይሁዳውያን ከሮሜ ጦር ጋር ተዋግተው የሞቱት ሲሞቱ የተረፉት እርስ በእርስ ተቀራደው ከመማረክ ሞትን በመረጡበት ሰዓት ጆሴፈስ እና ሁለት አይሁዳዉያን ብቻ መገዳደል እንደሌለባቸው ተማምነው እጃቸውን ለሮሜ ጦር ሰጥተዋል:: ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ለሮማውያን ምርኮ በመሆን ከወገኖቹ ተነጥሎ መረጃ እየሰጠ በቁም እስር እስከ እድሜው ፍፃሜ ኖሮአል:: በመዘመኑም ብዙ መጽሐፍቶችን ጽፎአል::

ጆሴፈስ በፃፈው የአይሁድ ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያው ጽህፈት ቄሬኔዎስ በሶርያ ተሹሞ ሳለ የተቆጠረ ሲሆን እንደ አውሮፓውያኑ ግሪጎሪያን አቆጣጠር በ7 ዓመተ እግዚእ እንደሆነ ያሳያል:: ይህ ደግሞ በመጀመሪያይቱ ጽህፈት (ቆጠራ) በ7 አመተ እግዚእ ከሆነ የምእራባውያኑ ዘመን መቆጠሪያ በ7 አመት ቀድሞ ሄዶአል ማለት ይሆናል:: ከላይ ባየነው መሰረት የግሪጎሪያኑ ዘመን መቁጠሪያ ባይታመንም



ይህን ቁጥር ወስደን ከኢትዮጵያዊው ዘመን መቁጠሪያ 2000 ዓ.ም./2001 ዓ.ም. ላይ ስንደምረው 2007/2008 ይሰጠናል ማለት ነው::[1] ይህ ማለት ደግሞ ምእራባውያኑ ጌታ ሲወለድ 7 አመተ እግዚእ ብለው ቆጥረዋል ማለት ነው:: ጆሴፈስ ባመላከተው መረጃ ደግሞ ከምራባውያኑ 2007/8 ላይ 7 አመት ስንቀንስ 2000/2001 ዓ.ም. እናገኛለን በዚህም የኛ ዘመን አቆጣጠር ትክክለኛ እንደሆነ የተረዳ ይሆናል::

ጆሴፈስ ስለ ጌታ የፃፈው አንቀፅ ደግሞ በይበልጥ ትኩረት የሚሰጠው ነው የእርሱ አገላለጽ ሳይዛባ እንዳለ ሲነበብ እንዲህ ይላል::

«በዚህ ጊዜ ኢየሱስ የሚባል የጥበብ ሰው ነበር» «ሰው» ነው ለማለት የምንችል ከሆነ ነው ምክንያቱም ታላላቅ ተአምራት ሰሪና እውነትን ሰባኪ ስለ ነበር አሕዛብንና አይሁዳውያንን በትምህርቱ ወደራሱ አምጥቶአቸው ነበር::

---

1. የኛና የግርጎሪያኑ ዘመን አቆጣጠር በ7 አመትና በ8 ይለያያል በኛ አዲስ አመት መስከረም ሲገባ በ7 አመት ግርጎሪያኑ ይቀድመን የነርሱ ጥር ላይ ሲውል በ8 ይቀድመናል በገና እለት አመት ያለመለወጣቸው ክርስቲያናዊ ዘመን አቆጣጠርን የተከተለ የአመት ለውጥ የላቸውም ያስብላል:: ስለዚህ በሁለት አመቶች (1999/2000 ወይም 2000/2001) እያሉ ማስቀመጥ ያስፈልጋል::

እርሱም ክርስቶስ ነበር ጲላጦስም ከኛ ሰዎች (አይሁዳውያን) መካከል ታላላቆቹ (ሃና እና ቀያፋ) በመከሩት ምክንያት በመስቀል ይሞት ዘንድ አዘዘ::
የሚወዱትም የሞተ መሰሏቸው ነበር (ደቀ መዛመርት) በሦስተኛው ቀን ግን ህያው ሆኖ ታያቸው ይህም ነብያት አስቀድሞ እንደ ተነበዩት ሆነ:: ከዚህ ውጭ አስር ሺህ የሚያህሉ ታምራቶችን እንደስራና በርሱም የተጠሩ ክርስቲያን የሚባሉ ቡድኖች መመስረታቸው እስከዛሬ ይታወቃል::» ይላል

ምንም እንኳን አንዳንዶቹ ይህ መጽሐፍና ጽሁፍ በክርስቲያኖች የተደረሰ ነው ለማለት ቢደፍሩም ቅሉ ግን ማንም ምንም ቢያደርግ ሊያዛባው የማይችል እንደ ብረት የጠነከረ ማስረጃያ ስለመሆኑ ግልጽ ነው:: አስር ሺህ ታምራቶች ከተባሉት ውስጥ በወንጌል፣ ተአምረ ኢየሱስ እና ተአምረ ማርያምን ጨምሮ ስንቆጥር የተጠቀሰውን ያህል እንደሚመላ መረዳት እንችላለን:: ከነዚህም አንዳንዶቹ ከባድ ከመሆናቸው የተነሣ ፍፁም እምነት የሌለው ሰው እንዳይደናቀፍ እና ሰውም ደግሞ ጎደሎ ነውና እንዳይስት ቅዱስ ዮሐንስ እንዲህ እያለ መፃፉን ማስተዋል አለብን::

«ከዚህ መጽሐፍ ውጭ ደግሞ ያልተፃፉ ኢየሱስ ያደረጋቸው ብዙ ተአምራቶች አሉ» (ዮሐ. 20፣ 30-31) ኢየሱስ ያደረጋቸው ተዓምራቶች በሙሉ ተዘርዝረው ይፃፉ ቢባል ሰማይ እንደ ብራና ባህርም እንደ ቀለም ቢሆን ባልበቃ ነበር:: (ዮሐ. 21: 25)

ከላይኛው ጥቅስ ላይ ወንጌሉን «አንድ መጽሐፍ» ብሎ ሌላ መጽሐፍ አለ ያለው ተአምረ ኢየሱስን ሲሆን እርሱንም ቅዱስ ዮሐንስ ደግሞ ጽፎታልና ሌላ መጽሐፍ አለ ሲል ቅዱስ ዮሐንስ ችሏል::

ጆሴፈስ ይህንንም መረጃም በማቅረቡ ስለ እውነተኛው ዘመን አቆጣጠር ዋነኛው ምንጭ በመሆን ለአለም ባለውለተኛ ያደርገዋል:: ስለሆነም እርሱ ያስቀመጠው መረጃ ከኢትዮጵያውያኑ ዘመን አቆጣጠር ጋር የሚጣጣም እና የሚገናኝ እንጂ ለሌላ ለማንኛውም ዘመን አቆጣጠር አመላካች ሊሆን እንደማይችል በቀላሉ መገንዘብ እንችላለን::

## ምዕራፍ አስር

## አቡነ አውሳቤዎስ ስለ ጌታችን ልደት የገለፀው ማስረጃ

አውሳቤዎስ የቤተክርስትያን ታሪክ አባት ይባላል:: ይህም ስለ ወንጌልና ስለ ቤተክርስትያን ከክርስትና በአለም ሁሉ መሰበክ በኋላ አስፍቶና አጉልቶ ለመፃፍ ቀዳሚ ስለነበረ ነው:: እርሱም እንደ አንድምታ ወንጌል ትርጓሜ መግቢያ መጽሐፍ ቅዱስን በዘር፣ በአንቀጽና በምዕራፍ እንደቆጠረም ተጽፏል:: ትሩፋቱም ብዙ ከመሆኑም የተነሣ ርእሰ ሊቃውንት ሊባል ይገባዋል:: ዛሬ ድረስ በእርሱ ተጋድሎ መጽሐፍት እንዳይበረዝ፣ ዝንጋኤ ታሪክን ከማወቅ ወደ ኋላ እንዳያስቀረን አድርጓልና:: አውሳቤዎስ ስለ ጌታችን ልደት ያሰፈረልን መረጃ አለ:: ይህም መረጃ ስለ ጌታ ልደት ዘመን በሦስት ወገን ሲመሳከር ወደ አንድ አይነት አመት የሚያመላክት አድርጎ አስቀምጦታል::

አውሳቤዎስ እንደፃፈው ስለ ጌታችን የልደት ዘመን ይህንን ብሎአል::

« [ጌታችን የተወለደው] በአርባ ሁለተኛው አመተ ንግስና ለአውጉስጦስ እንዲሁም ግብጽ በገበረችበት እና አንቶኒ እንደሁም ኪሊዮፓትራ ከሞቱ በሀያ ስምንተኛው አመት ሲሆን የተሎሜ ስርወ መንግስት ያበቃበት ቂሬኔዎስ ደግሞ በሶሪያ



ደጅአዝማች ሆኖ የመጀመሪያው ጽህፈት በተቆጠረችበት ዘመን ነው» ይላል

አውሳቤዎስ ያስቀመጠው መረጃ ከቀድሞ ምዕራፍ ጋር እንደታየው ቂሬኔዎስ በሶርያ ደጅአዝማች ሲባል የመጀመሪያው ጽህፈት (ቆጠራ) ሆነ ብሎ ያስቀመጠውን ሰባት አመተ እግዚእን ያካትታል::

በማስቀጠልም በአርባ ሁለተኛው አመት አውግስጦስ ከነገሰ ሲል ሌላ ወደ እዚሁ አመት የሚያመላክት አቆጣጠር ያስቀምጣል:: ብዙዎቹ እንደሚስማሙት አውግስጦስ በ27 ቅ.ል.ክ ነገሰ ብለው ይናገራሉ:: ነገር ግን ከዚህ በእጥፉ በራቀ ሁኔታ ታሪክ ሲያስረዳ በዚያን አመት የሮሜ ምክር ቤት (Senate) አውግስጦስ (Augustus) የሚለውን የክብር ማዕረግ እንጂ ሌላ እንዳላደረገለት ግልጽ ይሆናል:: አውግስጦስም ማለት «የከበረው» የሚል ማዕረግ እንጂ ከስልጣን ጋር የተያያዘ አይደለም:: በእላይኛው አመት 27 ቅ.ል.ክ ላይ ተነስቶ ቢቆጠር አርባ ሁለት አመት የጌታ ልደት በ14 ዓመተ እግዚእ ላይ ያደርገዋል ይህ ደግሞ ከመጀመሪያው ጽህፈት በ7 ዓመት የቀደመ ነው:: (በ7 ዓመት መቅደሙን ልብ በል) የሰባት አመት ልዩነቶች መኖራቸውን ካስተዋልን እንዲሁም ወደ ፊት 7 ዓመት የተሻገሩ (ቅድመ ልደት B.C.) ሳይሆን (በዓመተ እግዝእ A.D.) መሆናቸው ተያይዞ በኢትዮጵያዊያንና በግሪጎሪያውያን መካከል ያሉትን የቀደሙት ሰባት ዓመት

ልዩነቶች እንድናስተውል ያስገድደናል:: አውግስጦስ በመጀመሪያ ጊዜ በሮሜ ሀገር ልማድ እንደነበረው የምክር ቤቱ መሪ ተናጋሪ ሆኖና ንግስና በሚመስል ሁኔታ ታላቅ ሹመት የተሾመው ኮንሱል (Consul) በመባል በጥር (January) አዲስ አመት ከመግባቱ ጀምሮ በ34 ቅ.ል.ክ ጀምሮ ነበር:: [1] እዚህ አመት ላይ 42 ስንጨምርበት ስምንት አመተ እግዚእን እናገኛ ለን:: ይህም ከላይኛው መረጃ ወይም ከመጀመሪያው ጽህፈት በሰባት አመት እግዚእ መሆን ጋር ይጣጣማል::

የኢትዮጵያውያንና የምዕራባውያን አቆጣጠር ልዩነቱ 7 እና 8 ዓመቶች መሆናቸው ዋነኛው ምክንያት እነርሱ ቀድመው ከታህሳስ 28 አንድ ብለው ጀምረው እዚያ ሲመለሱ አመት ሲያደርጉ (አመት ሲሞላላቸው) እኛ ደግሞ መስከረም አንድን እየጠበቅን አንድ አመት የማለታችን ጉዳይ ነው:: በዚህም እኛ ወይም እነርሱ ቀደሙ ለማለት 532 አ.እ. ላይ የተወሰነው አመትን ከእኛ ጋር አብሮ ማየት ያስፈልጋል:: ሁለቱ አመቶች ማለትም የኛ ዓመተ ምህረትና በዲዮናሲዮስ የተወሰነው አመትን አይቶ 7 አመት ወይም 8 አመት ልዩነት አለ ማለት ይቻላል:: አሊያ ግን በደፈናው የጠራው ልዩነት 7 አመት ወይም 8 ነው ለማለት ያስችግራል::

---

1. See the dictatorship of Julius Caesar, Jemes, Brestad; **Ancienit Times. The history of the old world** (Jim and company, 1916) p. 591; See also wikipedia the free encyclopedia S.V. **Augustus** p. 16




ሶስተኛው የአውሳቤዎስ መረጃ የጌታችን ልደት ሮማውያን ግብጽን ሙሉ በሙሉ ከተቆጣጠሩ በኋላ እና የክሊዮፓትራና የማርክ አንቶኒ ሞት በኋላ 28 ዓመቶች ሲደመሩበት የጌታ ልደት ዘመን ነው ብሎአል:: በአክቴቪያንና በአንቶኒ መካከል በተደረገው የባህር ላይ ውጊያ የግብጽ ሀይል የነበረው የአንቶኒና የኪሊዮፓትራ ጦር ተሸንፏል:: ይህ እንግዲህ የአክቲዮም ጦርነት በመባል ሲታወቅ በ31 ቅ.ል.ክ እንደተደረገ ይነገራል:: በአመቱ በተደረገ የግብፅ ወረራ (በ30 ቅ.ል.ክ) አንቶኒና ኪሊዮፓትራ በመሞታቸው ግብፅን የመቆጣጠሩ ስራን አክቴቪያን ይያያዘዋል::

በሂደቱ ግን በራሱ አጐት ከኪሊዮፓትራ የተወለደው ቄሳርዮን የተሰኘው ልጅ የስልጣኑ ባላንጣ እንደሆነ በመረዳት ከተደበቀበት ስፍራ አድኖ ለመያዝ ፍለጋውን አጧጧፈው:: በዚህም ድርጊቱ ላይ ጥያቄ ላነሱበት ሰዎች «ሁለት ቄሳሮች ለአለም ብዙ ናቸው አንድ ብቻ ይበቃል» በሚል ሽሙጥ የተቀመመ ነበር:: በአመት ወይም በሁለት አመት ውስጥ ገና ልጅ የነበረውን ቄሳርዮንን በመያዝ ሊገድለው ችሏል:: ይህ እንግዲህ ወደ 29 እና 28 ቅ.ል.ክ ያደርሰናል:: ነገር ግን ግብፅ የተረጋጋች ሀገርና ሮማውያን ሙሉ በሙሉ የተቆጣጠሩዋት ለመሆን ብዙ ዘመን እንደሚፈጅ ግልጽ ነው ካለፉት ማስረጃዎች ላይ ስንነሣ የሚመጡት 7/8 ዘመኖች በየቦታው የማስገበር ትግል ቢካሄድበት የግብፅ መገበረ ወደ 20 ቅ.ል.ክ

ሊጠጋ ነው ማለት ነው:: ይህ እንግዲህ ጥልቅ የሆነ የጥናት ክፍል ሲሆን «ግብፅ ሙሉ በሙሉ የተያዘችበት ዓመት ይህ ነው!» የሚል ድምዳሜ እስካልተደረሰ ድረስ መረጃውን በቅጡ ለመተርጐም ይቸግራል:: ነገር ግን ወደ ታች እየወረደ (ከ30 በታች) መሄዱ ግን አያጠራጥርም ስለሆነም ከዚሁ ላይ 28 ዓመት ሲቀንሱበት 1ኛውን አመተ እግዚእን ያለፈ አመት እንደሚያሳይ እርግጥ ነው:: በመሆኑም የጐርጐርያውያኑ ዘመን አቆጣጠር ወደፊት የቀደመ ነው ለማለት ያስችላል:: በቀላሉ በሂሳብ አቀማመጥ ግብፅ በላይኛው ማመላከቻ ሲገመት በ20? ቅ.ል.ክ ብትያዝ፤20 ቅ.ል.ክ + 28 ዓመት = 8 አመተ እግዚእ ይሰጠናል ማለት ነው::

እነዚህ መረጃዎች ሁሉ በቀላሉ እንደሚያመለክቱት የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር በትክክለኛው የጌታ ልደት ዓመት ላይ መመስረቱን ያረጋግጣሉ ይህ በሚቀጥለው ስዕላዊ መረጃ ሲቀመጥ የሚከተለውን ይመስላል::






*ስዕል 15፣ የአወሳቢዎስ የጌታ የሶስቱን ጌታ የልደት ዘመን እንዲሁም የታሪክ ማመልከቻዎች*

በነዚህ መረጃዎች መሠረት ምእራባውያን ጌታችን ተወለደ ብለው መቁጠር የጀመሩት በ7/8 ዓመት ቀድመው መሆኑን በግልጽ ያሳያል:: በዚህም የትኛው ዘመን መቁጠሪያ ትክክለኛ የትኛው ስህተተኛ መሆኑን መረዳት ይቻላል::



## ምእራፍ አሥራ አንድ

### ሊቁ ገማልያል ስለ የገሊላው ይሁዳ እና የፅህፈት ዘመን የተናገረው ማመልከቻ

በሐዋርያት ሥራ ምእራፍ 5 ከቁጥር 35-38 ላይ እንዲህ የሚል ቃል አለ::

> «ስለ እነዚህ ሰዎች (ሐዋርያት) ምን እንደምታደርጉ ተጠንቀቁ:: ከዚህ ወራት አስቀድሞ ቴዎዳስ 'እኔ ታላቅ ነኝ' ብሎ ተነስቶ ነበርና አራት መቶ የሚያህሉ ሰዎችም ከእርሱ ጋር ተባበሩ:: እርሱም ጠፋ የሰሙትም ሁሉ ተበታተኑ እንደ ምናምንም ሆኑ ከዚህ በኋላ ሰዎች በተጻፉበት ዘመን የገሊላው ይሁዳ ተነሳ:: ብዙ ሰዎችንም አሸፍቶ አስከተለ:: እርሱም ጠፋ የሰሙትም ሁሉ ተበታተኑ::»

ገማልያል ይህንን የተናገረው አይሁድ በሐዋርያት ላይ መከራን በማፅናታቸው የተነሳ ነበር በዚያን ዘመን ሐዋርያት በታላላቅ ተአምራት ስራቸው የተነሳ ኢየሩሳሌም በትምህርታቸው እንድትሞላ አድርገው ነበር:: የኦሪት መስዋትና እምነት እያለፈ መሆኑን የተረዱት አይሁድ ሐዋርያትን ለመግደል እየተማከሩ ሳሉ ነበር ገማልያል የተሰኘ ው የኦሪት ሊቅ ከላይ ያነበብነውን ጥቅስ የተናገራቸው::

በጥቅሱ ላይ እንደምንረዳው 'የገሊላው ይሁዳ' የተባለው ሰው ሮማውያን የእስራኤልን ሰው ሁሉ ለግብር በሚቆጥሩበት ዘመን ተከታይ በማብዛት ለእግዚአብሔር እንጂ ለሮሜዎች ግብር ልንገብር አይገባም ብሎ ታላቅ ጦርነትን ከሮሜዎች ጋር አስነሳ ታሪኩን ፍላቪየስ ጆሴፈስ እንደዘገበው እንዲህ ይነበባል::

> «በዚያን ዘመን የአርኬላዎስ ግዛት የነበረው የይሁዳ ክፍል ወደ ወረዳ ደረጃ ዝቅ አለ:: ኮፓኒየስ የሮሜ ፈረሰኛ ጦር መሪ የነበረው የገዢ (ፕሮኩራተር) መአረግ ይዞ በሰዎችም ላይ የህይወትና የሞትን ስልጣን ከቄሳር በእጁ እንዲሆን ተቀብሎ መጣ:: ኮፖኒየስ በሚያስተዳድርበት ጊዜ አንድ ገሊላዊ ስሙም ይሁዳ የተባለ የሀገሩን ሰዎች ያሳምፅ ዘንድ ተነሳ እርሱም ለሮማውያን እንደ እግዚአብሔር ከገበራችሁ ፈሪዎች ናችሁ እንዴት ለተራ ሰዎች ትንበረከካላችሁ እያለ አነሳሳቸው» በማለት ታሪኩን ይገልፃል::[1]

---

[1] The war of the Jews books 2 chapter 8 section one; see also chapter 17 section 8 for the second quotation.



በዚህ ገፀ ንባብ ላይ እንደምንረዳው ኮፖኒየስ የተባለ የሮሜ ፈረሰኛ ጦር መሪ ስልጣን ሲይዝ በፀሀፊትም ይቆጠሩ ዘንድ ትእዛዝ ከቄሳር (አውጎስጦስ) ሲወጣ ከሶሪያ የሁሉ የበላይ የነበረው ቄሬኔዎስ ደጃዝማቹ ትእዛዚቱ መፈጸምዋን በሚቆጣጠርበት ወቅት ጌታ ተወልዶአል:: ይህንን ጊዜ ጆሴፈስ ሲገልፀው በ6/7 አ.ም. ላይ ነበር ብሎአል:: ይህ ገፀ ንባብ የሉቃስ ወንጌልን የጌታ ልደት መረጃን ከመሰከረ በኋላ ሌላ ከማቴዎስ ወንጌል ጋር የሚያያዝ ወሳኝ መረጃን በዚሁ መፅሀፍ ላይ በምእራፍ አስራ ሰባት ቁጥርም 8 ጆሴፈስ እንዲህ በማለት ይገልፀዋል::

> «የገሊላው ይሁዳ ልጅ ምናሴም ዋና የሆኑትን የአይሁድ ሰዎች ይዞ ወደ ማሳዳ ምሽግ አቀና (የገሊላው ይሁዳ አይሁድን ቄሬኔዎስ በግፈበት ዘመን የወቀሳቸው እና እንዲያምፁ ያደረገው ነው:: እርሱም ዋና አታላይ ሲሆን እንደ ነብይ ለማስመሰል የሚሞክር ነበር:: አይሁድንም ከሮማውያን በፊት ለእግዚአብሔር እንዲገብሩ እንዲገባቸው የሚናገራቸው ሰው ነበረ) በዚያም የነበረውን የንጉስ ሔሮድስን የጦር እቃ ግምጃ ቤት ሰብሮ መሳሪያውን ለተከታዮቹና ለወንበዴዎች አደለ:: እንደ ንጉስም ታጅቦ ወደ ኢየሩሳሌም መጣ:: የአመፁም መሪ ሆኖ ከተማዋ እንድትከበብ ትእዛዝ ሰጠ:: ግንቡን ለመናድ ግን የሚያስፈልገው መሳሪያ አልነበራቸውም:: ወደ እርሱም

በተጠጉ ጊዜ የጦር ፋላፃዎች በላያቸው ላይ ከላይ ይለቁባቸው ጀመር (ሮሜዎች) በዚህም ምክንያት ከሩቅ ቦታ ጀምረው ውስጥ ለውስጥ መሬቱን እየቆፈሩ መሰረቱን ሊያናጉ ተጉ:: በመሰረቱም ላይ በደረሱ ጊዜ የሚቀጣጠል ጨምረው እሳት አነደዱ:: መሰረቱም ነዶ ሲያልቅ ግንቡ ፈረሰ:: ከውስጥ ያሉት ሮሜዎች ግን የሚያደርጉት ገብቶአቸው ሁለተኛ ግንብ ገንብተው ቆዩአቸው:: የሆነውንም ባዩ ጊዜም በጣሙን ተበሳጩ ከውስጥ የነበሩት አይሁዳውያንና የአመጽ ተባባሪዎቻቸው ከእነርሱ ጋር ይቀላቀሉ ዘንድ ሮሜዎቹን ስለወተወቱ ስለበዙባቸውም ይወጡ ዘንድ ፈቀዱላቸው የከተማዋም በር በተከፈተ ጊዜ ከውጭ የነበሩ የምናሴ ተከታዮች ወደ ውስጥ ዘልቀው ገቡ:: የሮሜ ወታደሮችም ተስፋ ቆርጠው ሀሞታቸው ፈሶ ነበር:: እየሸሹም ወደ ቤተ መንግስት ግንብ ገቡ የምናሴም ወገኖች የያዙዋቸውን ወታደሮች ገደሉ በመንደራቸውም ያለውን ዘርፈው አቃጠሉ::»

እንዲህም እያለ በጌታ ልደት ጊዜና በዋዜማው የነበረውን አመፅ ይገልፃል:: በዚህ መረጃ (evidence) እንደምንረዳው የገሊላው ይሁዳ በአመፀበት ዘመን ቄሬኔዎስ ቆጠራ የሚያደርግበት እንደሆነ ይታወቃል:: በሌላ በኩል ደግሞ ሄሮድስ ያልሞተና ገዢ የነበረበት ዘመን መሆኑንም



እንመለከታለን:: ይህ እንዴት ይታወቃል ቢሉ «የንጉስ ሄሮድስ የጦር እቃ ግምጃ ቤቱን ምናሴ በሩን ሰብሮ መሳሪያውን ለተከታዮቹና ወንበዴዎች አደለ» ያለውን በማምጣት ይፈታል:: ሄሮድስ ሞቶ ቢሆን ኖሮ 'የንጉስ ሄሮድስ' ብሎ ግምጃ ቤቱን ባልጠቀሰም ነበር በዘመኑ የነገሰው ይወርሰዋልና የእርሱን ስም በጠራ ነበር:: አሊያም ሮማውያኑን ጠቅሶ በእነርሱ እጅ የነበረው የጦር ግምጃ ቤት ባለ ነበር:: ስለዚህ በሁለቱም ገለፃዎች ሉቃስንና ማቴዎስን በሚስጥራት ያስታርቃል:: ሉቃስ ስለ ቄሬኔዎስ፣ ስለ ጽህፈት (ግብር) ቢፅፍ ማቴዎስ ደግሞ ስለ ሄሮድስ፣ ስለ ሰብአ ሰገል ስለ፣ ጦር በኢየሩሳሌም መጠንከር ይፅፋልና ነው::

የጌታችንን ታሪክ ልብ ብለን በወንጌል ገላጭነት ከመረመርን ደግሞ በኋለኛው ጊዜ አይሁድ ታሪክ እየጠቀሱ ጌታን ለመክሰስ ይህችውን የፅህፈት ዘመን አመፅን ተጠቅመውባታል:: እንዴት ይታወቃል ቢሉ ጌታችን አይሁድን ስለ አምላክነቱ ቢናገራቸው ታሪክ ጠቅሰው ለተንኮል ለክህደት እና ለክስ ይችኩሉ ነበር:: ለምሳሌም 'ጌታችን ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት በሶስት ቀን አነሳዋለሁ' ብሎ ስለ ትንሳኤው ልእልና ስለ ስጋው ሞት ቢናገር አይሁድ ታሪክ ጠቅሰው ዘሩባቤል 46 አመት የገነባውን እኛ 30 አመት ያነፅነውን ሄሮድስም 2 አመት ያደሰውን እና ያሳመረውን ቤተመቅደስ እርሱ በ3 ቀን እሰራዋለሁ ይፍረስ ይላል እንዲሉት ማለት

ነው:: (አንድምታ ወንጌል ቅዱስ ዘ ዮሐንስ ምእራፍ 2 ቁጥር 19 ጀምሮ ተመልከት) በዚህም ዘመን ማለትም ጌታችን በተወለደበት ዘመን የሆነውን ታሪክ ለሮሜ መንግስት በማስታወስ (ሉቃ 23:1-25) እንዲሁም ጌታችንን 'የገሊላው ሰው' ይሉት ነበርና (ዮሐ 7:42፣ 7:53) ይህም እንደ ይሁዳ ዘ ገሊላ ወይም እንደ የሀገሩ ሰው ይሁዳ በእናንተ ላይ አመፃን ሊያስነሳ ይሻል ብለው ከሮሜዎቹ ጋር ሊያጋጬት በመመኘት ግብርን ለቄሳር ልንገብር ይገባልን? ወይስ ለእግዚአብሔር? ብለው አምላካቸውን ሊፈትኑ እና ሊሽነግሉ ሲነሱ ይታያል (ማቴ 22:15-22)

የጆሴፈስ መፀሀፍ ዘመናትን የሚጠቁም እንጂ ሂደቱን በዘመን አስተካክሎ ወጥ ያደረገ ተከታታይነትን (Cronological) የጠበቀ መጽሐፍ አይደለም:: በመሆኑም ይህንን ያልተረዱ ሰዎች ይህ ፅሁፍ ክፍል የተጻፈው አርኬላዎስ በነገሰበት ዘመን ታሪኩ ስለሚጀምር ከዚያን ጊዜ አንስቶ ስላለው ብቻ ይፅፋል ይላሉ:: ነገሩን ሳስተዋለው ግን ጆሴፈስ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የሚጣጣም ወሳኝ ማስረጃ ጥሎ በማለፍ 'እፁብ እፁብ' እንድንል አስገድዶናል:: ይኸውም የገሊላው ይሁዳ ባመፀበት ዘመን ቄሬኔዎስ በሶርያ ገዢ ነበር ይላል:: አያይዞም የመጀመሪያው ጽህፈት በሆነ ጊዜ አመፅ ተነሳ ሄሮድስ ንጉሱ ያስቀመጠውን የጦር እቃ ግምጃ ቤት የይሁዳ ልጅ ምናሴ በሩን ሰብሮ ዘረፈው እያለ ወሳኝና ቁልፍ



የሆኑ መረጃዎችን በማስቀመጡ ዛሬ ላይ ተመራመርን ያሉ ምእራባውያን የወንጌሉን ነገር ለማጥላላት ብቻ ሲሉ ሄሮድስ በጽህፈት ጊዜ ያልነበረ ወይም የሞተ ነው በማለት ዘመን አቆጣጠራቸው ትክክል እንደሆነ ወንጌላውያኑም የተሳሳቱ ለማስመሰል የሚሞክሩበት ብዙ ድርሰቶችን ደርሰዋል::

ሀቁና እና እውነታው ግን በዘመኑ በነበረ የታሪክ ፀሀፊ እንደፃፈው ወንጌላውያኑ አንዱ የፃፈውን ሌላው ሳይደግመው እንደፃፈ ዋና ማስረጃና ምስክር ሆኖ ተገኝቶአል:: በዚህም የምእራብያውያኑ ግምትና ትምህርት (ስለ ዘመን አቆጣጠር) ህፀፅ የተሞላ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ እንረዳለን::

## ምዕራፍ አስራ ሁለት

## በዘመን መቁጠሪያው ላይ ያለ ተቃውሞ

በ1997 ዓ.ም. በአዲስ ትሪቢውን ጋዜጣ ላይ ስለኢትዮጵያዊው ዘመን አቆጣጠር አስመልክቶ የጋለ ክርክር ተካሄዶ ነበር:: ክርክሩ በሁለት አንጃዎች መካከል ሲሆን አንዱ ቡድን ዘመን መቁጠሪያው አስፈላጊ ነው:: እንዲሁም ትክክለኛ እና የባህላችንን ታላቅነት የሚገልጽ ነው የሚል ሲሆን ሌላኛው ደግሞ ዘመን መቁጠሪያው ኋላቀር፣ የተንቀራፈፈና ከአለም ጋር በአግባቡ እንኳን እንዳንግባባ መሰናክል የሆነ ነው የሚል ነበር::

በጋዜጣው ላይ ከተፃፉት ጽሁፎችና ፀሐፊዎች ማንነት ስንነሣ ግን ይህ የአህጉራት ርቀት፣ የገንዘብ እጥረት፣ የሰዓት ጥበት ሳይገድባቸው በዘመን መቁጠሪያው የመቀጠል ወይም ያለመቀጠል እጣ የተከራከሩት ኢትጵያውያን ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር ብቻ መሆኑ ከማሳዘን አልፎ ያስተክዛል:: ከሌሎች ሀገሮች ተሞክሮና ልማድ በወጣ ሁኔታ በእኛ ሀገር ላይ ብቻ ያለው የራስን ባህል ተቃዋሚ ኢትዮጵያዊ ማንነት አገር በቀልን ሁሉ አንጓጣጭ፣ የነጮች የበላይነትን እና የባህል ታላቅነት መስካሪና አድናቂ ሰው መፈጠሩ ለነገረው ለሀገሪቱ መጭ እጣ ተስፋ አስቆራጭ መንፈሳዊ ጦርነት ሆኖ በህይወታችን እና በህይወቴ ታዝቤዋለሁ::



ምንም እንኳን በአብዛኛው እኛ ኢትዮጵያውያን በባዶ ሜዳ ላይ ኩራት ቢኖረንም (ኩሩ ሕዝብ) ብንሆንም ቅሉ ዛሬ ዛሬ ይህ እንኳን ብርቅ ሆኖ የተፈጠረው ትውልድ ስለአገሩ እና ስለ ሕዝቡ ታላቅነት ለመመስከር እንደ ትልቅ ሞት ቆጥሮ ሲብከነከን ሲንገሸገሽ እናየዋለን:: ይህ ታዲያ ሁል ጊዜ በለመድናት «የቀኝ ገዢዎች ቅስም ሰባሪ» የምትለውን ሐረግ በቅጡ እንድንመረምር ሊያስገድደን የሚገባ ጉዳይ ስለመሆኑ አያከራክርም::

ብሎም በገሀድ ቅኝ ከተገዙ አፍሪካውያን ወንድሞቻችን ይልቅ ዛሬ እኛ መንፈሳችንን ለነጮች ባህልና አስተሳሰብ ተንበርካኪ መሆኑ ከየት የመጣ ነው? ብለን ጥልቅ ጥናት ማካሄድ ይገባናል:: ከኢትዮጵያዊነት ይልቅ ጃማይካዊነት፣ ከአፍሪካዊነት ይልቅ ፈረንጅ፣ ከአበሻ ይልቅ አረብ መሆንን የመረጡት የኛው ጉዶች በጉያችን ሲተራመሱ አይቶ እንዳላየ ማለፉ ነገ የማንነት ግጭት (Identity Crisis) ውስጥ የገባና ሀገሩን ከችግር ሊያወጣ የማይችል የባእዳን ምቹ መሣሪያ ትውልድ እንዲመሠረት ምቹ አጋጣሚ መፍጠር መሆኑንም ማወቅ ይገባል:: ያ ሆነ ማለት ደግሞ ነጫጮቹ ሆነ ሌሎቹ ለዘመናት ብራቸውን እየረጩ የተፍጨረጨሩለት አላማ ተሳካ ማለት ነው «ይማህረነ ክርስቶስ» ከማለት ውጭ ምን መፍትሄ አለ::

የአስራው ምዕት በዓል እንኳን ከመከበሩ ዋዜማ ላይ አንዳንድ አክራሪ ቡድኖች «ማን ተወለደ ብለን ነው የምናከብረው» ወይም «ይህ ዘመን መቁጠሪያ መላውን ኢትዮጵያዊ አይወክልም» ሲሉ ተደምጠዋል:: በፕሮቴስታንት አለሙና በኢትዮጵያም ያሉ ክፍሎች በአብላጫው የሚጠቀሙት የግሪጎሪያውያን ዘመን መቆጠሪያ እንደሆነም ይስተዋላል:: ምንም እንኳን «ማን ተወለደና» ለማለት ባይደፍሩም ቅሉ ትክክለኛ የዘመን መቁጠሪያ ነው ለማለት ግን እንደማይበረቱ እንገምታለን ከበረቱም ደግሞ እሰየው መልካም በርቱበት የሚያስብል ይሆናል::

ሌሎች ክፍሎች ደግሞ እራሳቸው ግራ የተጋቡና ሌላውንም ግራ የሚያጋቡ ናቸው:: ከላይ ኦርቶዶክሳዊያን ነን ይላሉ በሌላ በኩል ደግሞ የቤተ ክርስቲያኗን ትምህርት ይቃወማሉ:: ከላይ «ለኢትዮጵያ ሀገሬ ፍቅር አለኝ!» ይላሉ በገሀድ ግን የነጮችን የበላይነት ያስተጋባሉ:: ለዚያም ይሰራሉ:: የሀገረን ባህል ወግና ስልጣኔ ያንኳጥጣሉ ይቃወማሉ:: ባለፈው ምእራፍ እንዳየነው እንደነዚህ አይነት ክፍሎች ዘመን መቁጠሪያው ይቀየር እስከማለት ደርሰዋል::

እነዚህ ሁሉ ክፍሎች የሚያወሱት አንድ ሀሳብ አለ ይኸውም የኢትዮጵያ ዘመን መቁጠሪያ አለም አቀፋዊ ለሆነው የንግድ፣ የእውቀት እና የፖለቲካ ሂደት መገልገያ ባለመሆኑ ይህንን ዘመን መቁጠሪያ መጠቀም ወደ ኋላ የሚያስቀር



ወይም ከሰለጠነው አለም ጋር አብሮ የማያራምድ ዘመን አቆጣጠር ሆኖ ይይዘናል የሚል ነው:: እንደ እውነታው ከሆነ በአሁን ሰዓት ምእራባዊያን ባላቸው የፖለቲካ የምጣኔ ሀብት እና የጦር የበላይነት በመጠቀም በመላው አለም ዘመን መቁጠሪያቸውን በውድና በግድ እያሸከሙ አብላጫው የአለም ክፍል ተጠቃሚው ሊሆን ችሏል::

ዛሬ ላይ ዘመን መቆጠሪያቸው የተዛባ መሆኑን ሲረዱ «ኢየሱስ ክርስቶስ የሚባል ጭራሹን አልተወለደም» «ዘመን አቆጣጠራችን መታደስና አለመ አቀፋዊ እንጂ ክርስቲያናዊ መሆን የለበትም::» በማለት ያሳሳቱትን አለም በማደናገር ወደ ለመዱት የባህል ወራራና የአይምሮ የቅኝ ግዛት ውስጥ ለማስገባት በተራ ክህደትና ውሸት ሲቀጥፉ ይታያሉ:: [1]

ነገር ግን እንደ ቻይና፣ ጃፖን፣ እስራኤል፣ ኢትዮጵያ፣ ግብጽና ሌሎች እስላማዊ ሀገሮች ይህንን ዘመን አቆጣጠር የማይጠቀሙ መሆናቸውን መረዳት ያስፈልጋል:: በዋናነት ግን ዘመን አቆጣጠራችን አንዳች እንኳን ከመሰልጠን የማያግደን መሆኑን በስርአት መረዳት አለመቻላችን ያሳዝናል:: ለመሆኑ ዘመን አቆጣጠር ከማደግና ከመበልፀግ ጋር ምን አገናኘው?

1 See Kenneth Harding **"Do any first century Historians mention the Jesus of Christianity** (Internet, 2002) p.p 1-3; J. M. Robertson, **The Silence of Josephus** (internet, N. D) pp. 1-4

የሚል ጥያቄ ብቻ ለእነዚህ ክፍሎች መወርወር እፈልጋለሁ:: የትኛውም ሀገር ከነበረበት አስከፊ የድህነት አረንቋና ማጥ ሊወጣ የቻለው ጠንክሮ በመስራቱ፣ ለህዝብ እድገት ተቆርቋሪ አመራር መኖሩ፣ የአገር ልማትን አስቀድሞ ከሙስናና ከግል ጥቅማ ጥቅም በፀዳ ሁኔታ የሚንቀሳቀስ ዜጋ በመብዛቱ ብቻ እንጂ በቀንና በወር አቆጣጠር የሰለጠነ ምንም ሀገር የለም:: ለኛም የሚያዋጣን ከእንቁ በላይ የሚበልጠውን ባህላችንን አጥብቀን ይዘን ወደ ስራ በመግባት በጥረት እና ያለማቋረጥ በመበርታት ለውጥ ማምጣት ብቻ ነው::

ካለፉት ምእራፎች እንደምንረዳው ከምእራባውያኑ ጎርጎርያውያን ዘመን መቁጠሪያ ላይ ከተገኘው የአሁኑ አመት ማለትም 2008 ላይ 8 ዓመት የቀደመበት ሲነሣ 2000 እንደሚመጣ ነው:: ይህ ደግሞ የኛውን ዘመን መቁጠሪያ ሌላው ሁሉ ቢቀር በጥቂት ማስረጃዎች (አንድም ይሁን) የታሪክና የሃይማኖት ፀሀፊዎች ባስቀመጡት ማመልከቻና ቅርስ መሠረት ትክክል መምጣቱን ማየት ችለናል::

ጐርጐሳውያኑ እራሳቸው ባደረጉት ምርምር ከነርሱ ጋር የሚገናኝም ወይም የሚቀራረብ ምንም አይነት ታሪካዊ ማመላከቻ አላገኙም:: ይህ እንግዲህ ታላቅነት መሆኑን ተገንዝበን ይሆን? ስንቶቻችንስ ይህንን ውድ ዘመን መቁጠሪያችንን በሚገባ እንጠብቃለን? እናከብርማለን? «ዘመን መቁጠሪያው ይቅር!» የሚለው ሀሳብ በቅጡ ሲያጤኑት



«በእጅ የያዙትን ወርቅ እንደ መዳብ ይቆጥሩታል» የሚለውን የአበው ብሂል ያስታውሰናልና ይታረም እያልን ወደ መደምደሚያው እናመራለን::

## መደምደሚያ

ፀሀፊው ይህችን ጽሁፍ ለመፃፍ የገፋፋው ነገር ቢኖር በሀገር ውስጥ ባለው ፀጥታ ምክንያት ነው። ይህ ፀጥታ ያልኩት ነገር ስለ ዘመን መቁጠሪያው ትክክለኛነት የማሳየትና የማስረዳትን ነገር ማንም ሲመሰክር ያለማዳመጥን ሁናቴ ለመግለጽ ነው። የውጭ ሀገር ጋዜጠኞች በማያገባቸው ገብተው ስለ ኢትዮጵያውያን ዘመን አቆጣጠር ያሻቸውን ተናግረዋል። በእኛ ዘንድ ደግሞ ምላሹ ፀጥታ ነበር። በቅጡ ስለ ዘመን መቁጠሪያችን የሚያስረዱ አባቶች ጠፍተውም አይደለም። አለም ሊደርስበት የማይችለውን መንፈሳዊ እውቀት የተቃኙ የጠሩ ሊቃውንት እነርሱ አለምን እረስተው አለምም በተለይ እነርሱን ረስታ እንደተርታ እቃ በየገዳማቱ በየበረሃው እየተሰደዱ የወደቁትን የት ዘንግተናቸው?

እኔ በበኩሌ ይህ ጽሁፍ ስለዘመን መቁጠሪያችን ሙሉ ማብራሪያ ይሰጣል የሚል ሀሳብ የለኝም ይልቁንም ትንሽ ነገር ይገፍ ወደ የማያልቀውና የማይጕድለው የአባቶች አንድምታ ለመድረስ ይህችን ጽሁፍ ጫጭሬ አባቶቼ በመልክ በመልኩ እያደረጉ ብራናውን እየዳመጡ ቀለሙን እየበጠበጡ መላውን ዓለም በዋናነትም እኛ ልጆቻቸውን በመገረም አፍ እንዲያስከፍቱ ማነሳሻ እንዲሆን ገፀ በረከት አድርጌ ለመስጠት እንጂ። በአሁኑ ጊዜ «ሚሊኒየም» የሚለውን ቃልና በተያያዥ አመተ ምህረቱ የ2000 መሆኑን ያልሰማ ቢኖር ጥቂት ነው።



ስለዘመን አቆጣጠሩም ይህ ነው ብሎ ማስረዳት የሚፈልግ በመጥፋቱ ይህ ጽሁፍ ተዘጋጅቶአል። ከብዙ በጥቂቱም የኢትዮጵያን ታላቅነት ይገልፃል ተብሎ ታስቧል ይህንን ስንል ታዲያ በአዲሱ አስራ ምዕት ወደ ጥንተ ሞገሳችን ለመሻገር እንጂ በባዶ ሜዳ እንደለመድነው ለመታበይ እንዳይደለ ተገንዘቡልኝ። ለመሆኑ እንዴት ነው በአዲሱ አስራ ምዕት ለውጥ የምናመጣው? ብለን ብንጠይቅ መልሱ የሚሆነው መጀመሪያ ስህተታችንን አውቀን ማረምና በጎ ሰዎች ወደ መሆን መምጣት ስንችል ብቻ ነው።

በተገላቢጦሹ ግን ዛሬም ቢሆን ከትላንቱ የተለየ ምንም አላየንም። ይህም ትላንት እንደነበረ እየተደራረበ ሄዶ ታላቅ ውድቀትን ወልዷል። ድህነት እስከ አጥንቱ ዘልቆ የገባ ማህበረሰብ፣ በጭካኔ እየተረገጠ የሚኖር ገበሬ፣ የጭቃ ሹሞችና የመንደር ባለስልጣኖች መጫወቻ እንዲሆን የተፈረደበት በሚመስል ሂደት ለዘመናት ስንንፏቀቅ ከርመናል። በዚህ ዘመን ደግሞ እድገት ማምጣት ሩጫው የሚደናቀፈው ከአገር ውስጥ እኛው በእኛው በምናደርገው ሹኩቻ ብቻ የሚፈፀም ሳይሆን ከአለም አቀፍ የምጣኔ ሀብትና የባህል እንዲሁም የፖለቲካ የበላይነትን ለማረጋገጥ በሚዳክሩ ሃይሎች የተንኮል መራወጥ ጭምር መሆኑ አሌ አይባልም። «በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ» እንዲሉ ይህን አለም አቀፋዊ ተጽእኖ በመቋቋም «ድሀ ሆናችሁ፣ ባርነታችሁን አምናችሁ፣

ባህላችሁን ጥላችሁ፣ ማንነታችሁን ክዳችሁ ኑሩልን» ለሚሉን ሁሉ ምላሽ ሊሆን የሚገባው እንደነ ቻይና እና ህንድ እነርሱን የሚቀናቀን እና የሚፎካከር የሀገር ልማት በማምጣት ሊሆን ሲገባ የባሰውኑ አብዛኛውን ጥፋት ፍፃሚዎቹ እኛው ለእኛው መሆናችን ከማሣዘን አልፎ ያንገበግባል።

ዛሬ የእያንዳንዱ ሰው ህይወት በውጥረት የተሞላ ነው። ሕዝባችን የቀን ውሎ የሌሊት አዳሩ ሁሉ በኑሮ ውድነትና፣ በስጋት፣ በፍቅር እጦት ነገ ስለ አለው ክፉ ቀን እየባዘነ የቁም ቅዥት ኑሮ ነዋሪ ሆኗል። ከድጡ ወደ ማጡ እንዲሉ ተስፋ የሚሰጡ ፍሬዎች ባለማየታችን ሁሉችን ወደ ተስፋ መቁረጡ ድንበር ተዳርሰናል። ይህ ሀገራዊ ቀውስን የመውሰድ ብቃት ያለው የምጣኔ ሀብት ድቀትና የገበያ አለመረጋጋት የፖለቲካ ትርምስን እንዳይፈጥር ብዙ መስራት የግድ ነው። አሁን ወሬና ሽንገላን በመጠቀም ጥሩን ህይወት እገፋለሁ ያለ ሰው ካለ በጣም ተሳስቷል። ይልቁንም አሁን ከጥላቻ ይልቅ መፈቃቀር፣ ከመበታተን ይልቅ መቀራረብ፣ ከሙስና ይልቅ ሕዝብን የሚጠቅም ስራ፣ ከልዩነት ይልቅ ልዩነትን በመነናገር መፍታት፣ ከስልጣን ወንበር ላይ የሙጥኝ ከማለት ይልቅ ስልጣን ወደ ማጋራት አስተሳሰብ ልንመጣ ይገባል።



ያለበለዚያ ሁካታ፣ ግጭት እና ጥላቻ ላይ የተመሰረተ እንቅስቃሴ ማንንም ሰው ወደ ማይጠቅም ጎዳና ሀገርን ይወስዳል እንጂ አንድም ሰው እንኳን እንደማይጠቀም ግልጽ ነው። እውነት ይመሰከር ከተባለ አንዳንዶች የተወለዱበትን ሀገርና ባህል ለከርሣቸው ሲሉ በመሸጥ በሆዳቸው እንደ እባብ የተሳቡ እና በመሬት ላይ እየተንከባለሉ ስለ ነጮች የዘመን አቆጣጠር የበላይነት፣ የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ኋላቀርነት የባሕረ ሐሳብ መጽሐፍት ጉድለንነት እናሳያለን ሲሉ ጽፈዋል። ተናግረዋል። መስክረውማል። ሌሎችም ይሁዳዊ በሆነ ሰብእና ወገናቸውን እና ሀገራቸውን እንደቁም ከብት ለጥቂት ዶላር አሳልፈው ለመሸጥ የማይራሩ ሆነው ተገኝተዋል። የባሰባቸው ደግዋ እራሳቸውን ለጊዜያዊ ጥቅም ብለው የምእራባውያን ርካሽ በህልና እርኩሰት ማጠራቀሚያ ገንዳ አድርገዋል። ይህም አንዱ ኢትዮጵያዊ ለሌላኛው ጥላቻ እና ጥርጣሬን እንዲያተርፈ ታላቅ ምክንያት ሆኖአል።

ይህ እንግዲህ ምን ያህል ከሀገር ውስጥ በራሳችን ድክመት ከድንበር ውጭ ላሉ ጠላቶቻችን የተከፈትነው ክፍተት እንዳለ ያመለክታል። አልፎ ተርፎ እያንዳንዳችን ጎራ ክፍለን ከመባላቱና፣ ከመጨቃጨቅ ውጭ ተቃራኒ የሆነውን ሀሳብ በጥሞና በማዳመጥ ሰፊው ህዝብን ሊጠቅም ወደሚችለውና አገርን ሊያሳድግ ወደሚችል ሐሳብ ላይ ብቻ በጋራ በማተኮር ስንረባረብ አይታይም።

ይህ ደግሞ ለጠላቶቻችን ምቹ አጋጣሚ ፈጥሮ የተያያዘውን ፍም በማራገባቸው በእያንዳችን ህይወት ላይ ስለነገው መራራ ቀን ከወዲሁ የነገሮችን ጉዞ በማየት እንድንጨነቅ አስገድዶናል:: ስለዚህ ነገር በፍፁም ተአምራዊ ሚስጢር ከገለፀው ከትንቢተ(እንባቆም 3-7) ቃል በቀር ምን ብሎ መናገር ይቻላል:: «የኢትዮጵያ ድንኳኖች ሲጨነቁ አየሁ::» ይህችን ቀን ለኔ መቼም ቢሆን ከዚህ ቃል ወጪ ሊገልጽልኝ የሚወደውን ያርቅልኝ::

የኢትዮጵያ ህዝብ በአለም ላይ ካለ ከማንኛውም ህዝብ ይልቅ ነፃነቱን የጠበቀ ታላቅ ህዝብ ነው:: ይህም የተቻለው በራስ ስራና ሀይል ሳይሆን በእግዚአብሔር ጽኑ ክንድ ነበር:: የኢትዮጵያ ህዝብ የዚያን ያህል በአለም ውስጥ ካለ ከማንኛ ውም ሕዝብ ይልቅ በባንዳዎች የተጠቃና፣ የተረገጠ፣ የተንገላታና፣ የተዋረደ ስለመሆኑ ታሪክ ምስክር ነው:: የሩቁን እንኳን ስንመለከት በጣሊያን የሚመራውን ዘመናዊ ጦር ያሣፈረ ሕዝብ ሀገሩን እና ወገኑን በምታውቀው ዮዲት የተፈታ ነበር:: ከግራኝ አህመድ ጋር በመሆን እየመሩና እራሳቸው እየወጉ ከእርሱ ይልቅ ይህ ነው የማይባል ጥፋትን ያጠፉ «ክርስቲያን» የነበሩ ባንዳዎች ብዙዎች ነበሩ (ካስታንሆዞ ተመልከት) ከጣሊያንም መጥፋት መልስ በኋላ አርበኞች ተሸረው ባንዶች ስለተሾሙ አዝማሪው፣



«ኢትዮጵያ አገሬ ሞኝ ነሽ ተላላ፤
የሰራልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ!»

ሲል ገጥሞ ዘመን የማይፍቀውን ምፀት እስከ ዛሬ ተክሎ አልፏል::

በውኑ የዚህስ አገር ባንዳዎች የተለዩ ናቸው ከሰው ዘር እንኳን የወጡ የማይመስሉ ባእዳን ፍጥረት (UFO) ይመስል ከህፃንነት እስከ ሽምግልና ባደጉበት ሕዝብ እና ሀገር፣ ወገንና ዘመድ፣ መንደርና ወንዝ፣ ወግና ባህል ላይ ይህ ነው የማይባል በደል ሲያደርሱ ከማየት በስተቀር የሚያሳዝን ነገር ምን አለ? ሌሎቹ ለእግዚአብሔር ክብር ለቤተክርስትያን ሞገስ ስጋቸውን ለረሀብ ሰውነታቸውን ለአረር በሰጡባት ሀገር ሌላው ደግሞ ቅዱሳን ንዋያቱን ለማዘረፍ፣ የእምነት አሻራውን ለማጉደፍ፣ ሰበብና ምክንያት የሚፈልግ ብቻ ሆኖ ይገኛል:: ከእርሱ ጊዜ በፊት ለም የነበረውን አፈር ሞልቶ የሚፈሰውን ጅረት ልምላሜ የተላበሰውን ምድረ ገነት ወደ በረሃ ለመቀየር የማይራራውንስ ምን ይሉታል? ከላይ ስታዩ የጠቆሩ ውስጣቸው ግን በለምጽ ነዶ ከገረጡ ከአፍሪካዊያንና ኢትዮጵያውያን ፈረንጆች እግዚአብሔር በምህረቱ ይሰውረን::

አባቶች «የወረት ፍቅር ለጊዜው ይደምቅ» እንዲሉ ነጮቹ ለጊዜው የብርና የወርቅ ገፀ በረከት ቢያዥጎደጉዱ የድለላና የሽንገላ ቃላቶቻቸውን ቢዘሩ የጭብጨባና የሀሰት ከበሬታን ቢቸሩን ምን ይረባናል:: በዚህ ምድር ሆነ በወዲያኛው ሰውን

መልካም ሥራው ብቻ ይከተለዋል ሕሊናው ደግሞ በስራው ሥራ እንዲዳኝ ያስገድደዋል: ታዲያ ነገሩ ይህ ሆኖ ሳለ ነጫጮቹ አታሞአቸውን ቢደልቁ በእጃቸው ቢያጨበጭቡ እሪታቸውን እያቀለጡ ዶላር ቢሸልሙን ምን ይጠቅመናል:: እንደ ሀምሌ ነጐድጓድ በምድሪቱ ላይ ያልፋል የኢትዮጵያም ድንኳኖች ሲጨነቁ ይኖራሉ::

ጨለማና መቅሰፍት፣ እረሀብ እና ጐርፍ፣ ጭንቀት እና ድህነት፣ እርዛት እና ጦርነት ያመሰው ማንነታችን ሁሉ ተወግዶ ኢትዮጵያ አረንጓዴ ምንጣፍ የተነጠፈባት የሰላም እና የእድገት፣ የብልጽግና እና የበረከት፣ የሥራ እና የፍቅር ሀገር እንድትሆን ሁሉም ሰው ዛሬ ላይ ቆሞ በሀቅና በቅን ልቦና በንፁህ ህሊና ሊጋደል ይገባል:: በአለም ላይ መልካም ሆነው ያለፉ ሰዎች ሁሉ ለወገናቸውና ብሎም ለሰው ልጅ በማሰብ በጐ ሥራን ያከናወኑት ብቻ ናቸው:: ሁላችንን እግዚአብሔር ይርዳን:: እንደእነርሱ ሰው ለመሆን!

## ተፈፀመ



# ዋቢ መጽሐፍት /Bibliography/

## 1) በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተፃፉ መጽሐፍት


- Compton's Encyclopedia S.V. 'Calendar' Chicago: University of Chicago. 1983
- Horniblow and Sullivan, The March of time: Mighty men and Deeds London: 1999
- Breasted, James. (PHD). Ancient Times: A History of the Early World. Boston: Ginn and company. 1916
- Hitti, Philip. History of the Arabs. London: Macmillan press LTD. 1970.
- Jhosephus, Flavious. The wars of the Jews Vol. II.
- Harding, Kenneth. "Do any First century Historians Mention the Jesus of Christianity. (internet source: atheists of sillion valley home page)
- Shamuel, safari. The History of Israel from ancient times to the Modern formation. Jerusalem: 1973

- Sergew, Hable Sellassie. Ancient and Medieval Ethiopian History to 1270. Addis Ababa: United printers. 1972
- Seven day Adventist Bible Commentary in Seven volumes. Vol. 5. S.V. 'Herod' USA: Review and Herald. 1956
- Taddesse, Tamrat. Church and State in Ethiopia 1270-1527. London: Oxford press.1972
- Trimingham, T. Islam in Ethiopia. London: Frank Cass, 1952
- Wikipedia the free encyclopedia S.V. Agustus casar
- World History (Vol. I) USA Armed forces Institute. Wisconsin: 1970



## 2) በአማርኛ ቋንቋ የተፃፉ መጽሐፍት

1. ሚኒሊክ መርእድ አለሙ፣ መጽሐፍ ቅዱስና ኢትዮጵያ፤ አዲስ አበባ፣ ኢሜጅ ፓብሊሺንግ፣ 1999 ዓ.ም
2. ሰማንያ ወ አሀዱ መጽሐፍ ቅዱስ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ማህበር፣ 1995 ዓ.ም
3. ስንክሳር በግእዝና በአማርኛ፣ አዲስ አበባ ትንሳኤ ዘ ጉባኤ፣ 1995 ዓ.ም
4. አስራት ገብረ ማርያም እና ገብረሕይወት መሐሪ፤ የዘመን አቆጣጠር፣ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1984 ዓ.ም
5. በእምነት ምትኩ፣ የኢትዮጵያ ታላቁ ሀብት ባሕረ ሀሳብ (የዘመን አቆጣጠር)፣ ባህርዳር፣ ባህር ዳር ዩኒቨርስቲ 1984 ዓ.ም
6. አንድምታ ወንጌል ቅዱስ በግእዝና በአማርኛ፣ አዲስ አበባ፣ ተስፋ ገብረሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ 1988 ዓ.ም
7. ተአምረ ማርያም፣ አዲስ አበባ፣ ተስፋ ገብረሥላሴ ዘብሔረ ቡልጋ ማተሚያ ቤት 1996 ዓ.ም
8. ተአምረ ኢየሱስ፣ አዲስ አበባ ተስፋ ገብረሥላሴ ዘብሔረ ቡልጋ ማተሚያ ቤት 1990

9. ተክለ ፃድቅ መኩሪያ፣ የኢትዮጵያ ታሪክ ከአክሱም እስከ ዛጉዌ፤ አዲስ አበባ ፤ብርሃንና ሰላም ቀ/ኃ/ሥ/ማ/ቤ/ት፣ 1966 ዓ.ም

10. ጌታቸው ኃይሌ፣ ባሕረ ሐሳብ የዘመን አቆጣጠር ቅርሳችን ከታሪክ ማስታወሻ ጋር፤ኮሌጅቪል፤ መጥምቀ ዮሐንስ ዩኒቨርስቲ፣ 1993 ዓ.ም

11. በሪሁን ከበደ፣ የዋልድባ ገዳም ታሪክ፣ አዲስ አበባ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1983 ዓ.ም



# እርማት

ገፅ- 16 ቁጥር 1 specific objective የተቆረጠ ነውና በአንድ ላይ ይነበብ
ገፅ-16 የመጀመሪያው ጥያቄ መጨረሻው ላይ "በእኛ ትክክል ይመጣል ወይ?" በሚል ይስተከል
ገፅ- 22 ያስፈልጋልስ የሚለው ወደ ያስፈልጋል[4]
ገፅ- 22 መጽሀፍ የሚለው በመጽሀፈ ይነበብ የመጨረሻው አንቀጽ መስመር 1
ገፅ- 24 ኢትዮጲያውያን የሚለው በኢትዮጵያዊያን ይነበብ አንቀጽ ሁለት መስመር 1
ገፅ- 24 የመጨረሻው መስመር ላይ "መሆኑን" የሚለው መውጣት አለበት አን.2 መ 10
ገፅ- 39 እርስችውን የሚለው በእራሳቸው በሚል ይነበብ አንቀጽ 1 መስመር 6
ገፅ- 42 አደም የሚለው በአዳም ይነበብ አንቀጽ 3 መስመር 3
ገፅ- 43 የስረዳናል የሚለው በያስረዳናል ይነበብ አንቀጽ 1 መስመር 4
ገፅ- 44 ስንተ የሚለው በሰንበተ ይነበብ ዳንኤል አንቀጽ 1 መስመር 1
ገፅ- 45 የደርገወዋል የሚለው በያደርገዋል ይነበብ 4 አንቀጽ 1 መስመር 8
ገፅ- 46 በሕረ የሚለው በባሕረ ይነበብ አንቀጽ 1 መስመር
ገፅ- 49 የ የምትለው ፊደል ከዲዮቅልጢያኖስ ላይ ጠፍታ ይነበብ
ገፅ- 52 የስጠናል የሚለው በይሰጠናል ይነበብ አንቀጽ 1 መስመር 2
ገፅ- 59 የተተመው የሚለው በየታተመው ይነበብ አንቀጽ 3 መስመር 3
ገፅ- 84 ተአምር የሚለው በተአምረ ይነበብ አንቀጽ 1 መስመር 7
ገፅ- 90 ማስመስከሪያው ተቆርጦ የመጀመሪያ መስመር በወዲያኛው ገጽ (91) ሆኖአል በመጀመሪያ መስመር ላይ ያለው ወደማጣቀሻው ገብቶ ይነበብ (It is part of the footnote)
ገፅ- 92 የተመለከተው የሚለውን በየተመለከተውን በሚል ይነበብ
ገፅ- 161 የምተችበትን የሚለው በየሞተችበትን ይነበብ 25 አንቀጽ መስመር 7
ገፅ- 111 አንዱ የሚለው በአንድ ይነበብ አንቀጽ 2 መስመር 2
ገፅ- 115 ሲደረግም የሚለው በሲደረግም ይነበብ አንቀጽ 2 መጨረሻ መስመር 1
ገፅ- 142 ለነገረው የሚለው በለነገው ይነበብ አንቀጽ 2 መስመር 9